
Ministry of Finance (MoF)





# በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ሰነድ





UN WOMEN

ይህ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ የተዘጋጀው ሰነድ በመጀመሪያ መጋቢት 2011 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የገንዘብ ሚኒስቴርና ዩኤንውመን ትብ ብር ታተመ። በዚህ ህትመት የተገለጸው ሀሳብ የአጥኚው አመለካከት እንጂ የተቋማቱን አመለካከት የሚወክል አይደለም።

የዚህን ህትመት ይዘት ትክክለኛነት እውነተኛነት ብሎም ከተለያዩ ጽሁፎች የተወሰዱ ሀሳቦች በተገቢ ሁኔታ ምንጫቸውን ለመጥቀስ የተደረገውን ጥንቃቄ የተሞላበትን ጥረት አንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ የገንዘብ ሚኒስቴርና ዩኤንውመን ስለህትመቱ ይዘት ትክክለኛነት ሀላፊነትን አይወስድም። በተጨማሪም በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የጽሁፉን ፍሬ ሀሳብ ወይም ይዘት በመጠቀም ብሎም ወደ ሌሎች ቋንቋዎች በመተርጎም ሂደት ላይ ምናልባት ሊፈጠር ስለሚችል ስህተት ሀላፊነት አይወስድም።

የአሳታሚው መብት በህግ የተጠበቀ ነው

በኢትዮጵያ የታተመ።

Ministry of Finance (MoF)

# በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ሰነድ

UN WOMEN

# ምስጋና

በገንዘብ ሚኒስቴር የስርዓተ-ፆታ ጉዳይ ዳይሬክቶሬት በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ላሉ የቋሚ ኮሚቴ አባላት የሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ ቱልኪት/toolkit/ ሰነድን ለማዘጋጀት ለተሳተፉትና ለተባበሩት፣ ለሴቶችና ሕጻናት ቋሚ ኮሚቴ፤ ለበጀትና ፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ፣ ለሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም ለዚህ ሰነድ ዝግጅት የጎላ ሚና ለተጫወቱ የፌዴራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና አገር አቀፍ አማካሪዎች ሁሉ ልባዊ ምስጋናውን ይገልጻል።

በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የቋሚ ኮሚቴ አባላት የፌዴራል መንግስት ባለበጀት መ/ቤቶች ዕቅድ፣በጀትንና የዕቅድ አፈጻጸምን ሲገመግሙ እንዲሁም ክትትል ቁጥጥር ሲያደርጉ ከሥርዓተ-ጾታ አተያይ አንጻር ለመገምገም፤ ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዳ እና የሥርዓተ-ጾታ ጉዳይ ምላሽ ሰጪ በጀት የአሰራር ማንዋል መሰረት ተደርጎ የተዘጋጀው ቱልኪት (Toolkit) ከዩኤን ውመን(Un Women) በተገኘ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቷል፤ ለዚህም የዩኤን ውመንን ድጋፍ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ያመስግናል።

በመጨረሻም በዚህ ሰነድ ዝግጅት ወቅት ለተሳተፉ ባለሙያዎች እና ገንቢ አስተያየታቸውን ለለገሱ አካላት በአጠቃላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከልብ ያመሰግናል።

# ምህፃረ ቃል

| | |
|---|---|
| ም/ቤት | ምክር ቤት |
| መ/ቤቱ | መስሪያ ቤቱ |
| መ/ቤቶች | መስሪያ ቤቶች |
| የዕ.ት.ዕ | የእቅድና ትራንስፎርሜሽን እቅድ |
| እ.ኤ.አ | እንደ ኤሮፓዉያን አቆጣጠር |
| ክ/ኢኮኖሚ | ክፍለ ኢኮኖሚ |
| ት/ቤት | ትምህርት ቤት |
| ጥ/አ/ኢ | ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ |
| የኢ.ፌ.ዲ.ሪ | የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ |
| ዓ.ም | ዓመተ ምህረት |

# ማውጫ


## ምስጋና I

## 1. መግቢያ 1

1.1. ሰነዱ ምንን በሚመለከት ነው? 1
1.2. ሰነዱ ያስፈለገው ለምንድን ነው? 2
1.3. የሰነዱ ተጠቃሚዎች እነማን ናቸው? 2
1.4. ሰነዱን መቼና እንዴት ነው መጠቀም የሚቻለው? 2

## 2. የሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የስርአተ ጾታ እኩልነት ኢላማዎች 5

## 3. የስርአተ ጾታ ጉዳይ እና ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ዝምድና 9

## 4. የምክር ቤቱ አባላት በጀትን ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ምላሽ ሰጪ ከማድረግ አንጻር እንዴት አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ? 13

4.1. በም/ቤቱ የበጀት ሂደት እንዴት ይከናወናል? 13
4.2. በጀትን በማጽደቅ ሂደት የም/ቤቱ አባላት በጀትን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር እንዴት መገምገም ይችላሉ? 15
4.3. የም/ቤቱ አባላት ከሥርዓተ-ፆታ ዕይታ አንጻር የኦዲት ግኝትን በተመለከተ ምን ማድረግ ይችላሉ? 19
4.4. የም/ቤቱ አባላት የፌዴራል መንግስት አካላትን በመከታተል እና በመቆጣጠር ስራቸው የስርአተ ጾታ እይታን እንዴት ማካተት ይችላሉ? 19

4.5. የም/ቤቱ አባላት ህግንና ፖሊሲን በማውጣት ሂደት ከስርአተ ጾታ አንጻር እንዴት መመርመር ይችላሉ? 21
4.6. የስርአተ ጾታ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች 23

**5. የማስፈጸሚያ ስልት** **27**
5.1. በሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ዙሪያ የም/ቤቱን አባላት ግንዛቤ ማሳደግ 27
5.2. በበጀት ዙሪያ የጥናት ውጤቶችንና መረጃዎችን ተደራሽነት 27
5.3. የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ ማካተትን ተቋማዊ ማድረግ 28
5.4. በተለያዩ ሀገራት ያሉ የፓርላማ አባላት የመካከለኛ ዘመን ማክሮኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ ዝጅግት ላይ ያላቸው ሚና 29
5.5. የም/ቤቱ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን አተገባበርና ክትትል ስራውን እንዴት ማጠናከር ይችላል? 29

**እዝል1:አንዳንድ ከበጀትና ከሥርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦች ምንነት** **31**

**እዝል2:ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ መሠረት የሚሆኑ ብሔራዊና ዓለምዓቀፍ መሳሪያዎች** **39**

**እዝል3:የተመረጡ ሴክተሮች ዋና ዋና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችና መፍትሄዎቻቸው** **45**



# ክፍል 1. መግቢያ

በጀት የመንግሥትን ፖሊሲ በአግባቡ ለማስፈጸም ቁልፍ ሚና ያለው መሣሪያ ነው፡፡ በተጨማሪም የመንግሥትን የፊስካልና የኢኮኖሚ ግቦችን እንዲሁም በማህበራዊ ዘርፉ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን አቅጣጫዎችም ያመላክታል፣በመሆኑም በሰዎች የዕለት ተለት ህይወት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

እንደሚታወቀው ሴቶችና ወንዶች በሀብት ተደራሽነትና ተጠቀሚነት፣ በማህበረሰቡ ውስጥ ካላቸው ሚናና ኃላፊነት እንዲሁም ከሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች አንጻር በተለያየ ሁኔታ ላይ የሚገኙ በመሆናቸው የተመደበው በጀት በእነዚህ አካላት ላይ የሚኖረው ተጽእኖ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል የበጀት አመዳደብ ሂደት እነዚህን በሴቶች እና በወንዶች መካከል ያሉ ልዩነቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ክፍተትን ለማጥበብ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህንንም ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ እንዲሆን በጀት አሰራርን በመከተል ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት በአጠቃላይ የመንግሥትን በጀት አመዳደብን (ሲታቀድ ሲጸድቅ፣ ተግባራዊ ሲደረግ፣ ክትትልና ግምገማ ሲደረግ) ከሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አንጻር ማየት ሲሆን፣ የሴቶችና የወንዶችን ልዩ ፍላጎቶችን፣ ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮችና የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ምላሽ መስጠት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ አሰራር በየደረጃው በሚገኙት የመንግሥት መዋቅሮች ወጪ እና የመንግስት ገቢ የሚሰበሰብበት መንገድ በሴቶች እና በወንዶች ላይ የሚያስከትለውን የተለያየ ተጽእኖ በመመርመር የበጀት አመዳደቡ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በሚያሰፍን መልኩ ተግባራዊ ስለመሆን ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡[1]

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ ረገድ ወሳኝ ባለድርሻ አካል ሲሆን፣ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራርን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ የማይተካ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሰነድ የም/ቤቱ አባላት የፖሊሲና የበጀት ግምገማ እንዲሁም ክትትል በሚያደርጉበት ወቅት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራር በአግባቡ ተግባራዊ ስለመሆኑ ለመገምገም እንደ አንድ መሣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው፡፡

## 1.1 ሰነዱ ምንን በሚመለከት ነው?

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በህግ ከተሰጡት ተግባራትና ሃላፊነቶች መካከል ህግን ማውጣት፣ በጀትን ማጽደቅ፣ አስፈጻሚ አካላትን መቆጣጠርና መከታተል ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ተግባራት ደግሞ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ሰነዱ ህግን በማውጣት ሂደት ውስጥ ም/ቤቱ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ጥሩ መደላድል ለመፍጠር ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ግንዛቤን ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ም/ቤቱ በጀትን በሚያጽደቅበት ሂደትም እቅድና በጀቱ ለስርአተ ጾታ ምላሽ የሚሰጥ መሆን እና አለመሆኑን ለመመርመር የሚያስችል ክፍልንም የያዘ ሰነድ ነው፡፡ ም/ቤቱ በክትትል እና ቁጥጥርም ወቅት የተቋማትን አፈጻጸም ከስርአተ ጾታ አተያይ አንጻር ለመመርመር የሚያግዝ ሰነድ ነው፡፡

1. ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (2005), ብሔራዊ ለስርዓተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት የአሰራር መመሪያ, አዲስ አበባ

## 1.2 ሰነዱ ያስፈለገው ለምንድን ነው?

ይህ ሰነድ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት፤ ፖሊሲ እና በጀትን ሲገመግሙ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ሲያደርጉ ከስርአተ ጾታ አተያይ አንጻር ጭምርም በመገምገም ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራርን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር የላቀ ሚና እንዲጫወቱ ለማገዝ የተዘጋጀ መሣሪያ ነው።

## 1.3 የሰነዱ ተጠቃሚዎች እነማን ናቸው?

የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ህግ የማውጣት እና የምርመራ እና ቁጥጥር ሥራዎቻቸውን ሲያከናውኑ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ባገናዘበ መልኩ እና ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ መሆን ይኖርበታል። በዚህም ምክንያት ሁሉም የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን በተግባራቸውና ኃላፊነታቸው ውስጥ አካተው መስራት እንደሚጠበቅባቸው ነው።

ስለሆነም ይህን ሰነድ በዋናነት የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች እንዲጠቀሙበት የተዘጋጀ ሲሆን፣ ሌሎች ከቋሚ ኮሚቴዎቹ ጋር የሚሰሩ ባለሙያዎች/አማካሪዎችም ሊገለገሉበት ይችላሉ። በተጨማሪም የፌዴሬሽን ም/ቤት ሰነዱን ከተግባሩና ኃላፊነቱ አንጻር በማሻሻል ሊጠቀምበት ይችላል።

## 1.4 ሰነዱን መቼና እንዴት ነው መጠቀም የሚቻለው?

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት ሰነዱን ህግን ለማውጣት እና በጀትን ለማጽደቅ ሲመረምሩ እንዲሁም የክትትልና የቁጥጥር ስራዎቻቸውን ሲያከናውኑ ከስርአተ ጾታ አተያይ አንጻር ለመመርመር መጠቀም ይችላሉ።

ሰነዱ በ5 ክፍሎችና በሶስት እዝሎች የተከፈለ ነው። የመጀመሪያው ክፍል ስለሰነዱ አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን ክፍል ሁለት ደግሞ በሁለተኛው የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ከስርአተ ጾታ አንጻር የተቀመጡ ኢላማዎችን የሚገልጽ ክፍል ነው። የም/ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች የሴክተሮችን እቅድና በጀት ሲገመግሙ እነዚህ የስርአተ ጾታ ኢላማዎችና የሴክተር የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በአግባቡ መካተታቸውን እንዲሁም በአስፈጻሚ አካላት ላይ ክትትል እና ቁጥጥር ሲያከናውኑ በአግባቡ መተግበራቸውን ለመቆጣጠር ይረዳቸዋል። በሌላ በኩል በፆታ የተለየ አመልካችና ዒላማ ያላስቀመጡ ሴክተሮችም ከተቋቋሙበት ተግባርና ሀላፊነት አንጻር የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት የሚያረጋግጡ አመልካችና ኢላማዎችን በመቅረጽ እየሰሩ መሆናቸውን መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ ነው።

በክፍል አራት ደግሞ የምክርቤቱ አባላት በጀትን ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ምላሽ ሰጪ ከማድረግ አንጻር እንዴት አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚችሉ በዝርዝር ያስቀምጣል። በዚህ ረገድ ለበጀት መነሻው ፖሊሲ ከመሆኑ አንጻር ም/ቤቱ ፖሊሲን ወይም በጀትን በማጽደቅ ሂደት ፖሊሲውን ወይም በጀቱን ከስርአተ ጾታ አንጻር እንዴት መመርመር እንደሚቻል በግልጽ ያስረዳል። በተጨማሪም ይህ ክፍል ም/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሲያከናውን ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑን እንዴት መመርመር እንደሚቻል ይገልጻል። ክፍል 5 ደግሞ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ አስቻይ ሁኔታዎችን ይዘረዝራል።

በእዝል 1 ላይ ስለ ሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ምንነትና ከሥርዓተ-ፆታ ጋር ተያያዥነት ያሏቸው አንዳንድ ጽንሰ ሀሳቦች የተቀመጡ ሲሆን፣ ሰነዱን በሚጠቀሙበት ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ መመልከት ይቻላል።

በጀት መንግሥት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (የዕትዕ) የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማስፈን የገባውን ቃል-ኪዳን ወደ ተግባር ለመቀየር አስፈላጊው መሳሪያ ነው። በመሆኑም ለበጀት መነሻ የሆኑትን ሀገራችን የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማስፈን ያወጣቻቸውን ሀገራዊ የፖሊሲ ማእቀፎች እንዲሁም በአህጉራዊ እና በዓለምአቀፍ ደረጃ የገባቻቸው ሥምምነቶች ዙሪያ ግንዛቤ መኖር አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ዋና ዋና ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችና አገር አቀፍ ማዕቀፎች በእዝል 2 ላይ የተቀመጡ ሲሆን፣ የሰነዱ ተጠቃሚዎች ሰነዱን ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት እዝሉን እንዲመለከቱ ይመከራል።

በተጨማሪም በጀት በተለያዩ ሴክተሮች ለሚታዩት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት ወሳኝ መሣሪያ እንደመሆኑ የም/ቤቱ አባላት በተለይም የዋና ዋና ሴክተሮች የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ግንዛቤ ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ለዚህም ም/ቤቱ የእድገት ተኮር ሴክተሮች ዕቅድና በጀት ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ለመገምገም እንደ ማገናዘቢያ የሚያግዙ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች በእዝል 3 ላይ ተዘርዝሯል። በእነዚህ የእድገት ሴክተሮች ላይ ማተኮር ያስፈለገው ሴክተሮቹ በሚሰጡዋቸው አገልግሎቶችና በሚያመርቱዋቸው ምርቶች የሴቶችን ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት በማሳደግ ሴቶች ከሀገራቸው ሀብትና እድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግና በማብቃት ሴቶች በኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዘርፎች የሚያበረክቱትን አስተዋጾ ለማሳደግ ሴክተሮቹ በአንጻራዊነት ያላቸው ተጽእኖ ከፍተኛ በመሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ የተጠቀሱት ሴክተሮችን እንደምሳሌ በመጠቀም በሌሎችም ሴክተሮች ላይ ከሴክተሮቹ ተግባርና ሀላፊነት አንጻር የሴክተሮቹን የስርአተ ጾታ ጉዳዮችን መለየት ያስፈልጋል። እንዲሁም እ.ኤ.አ 2017 ዓ.ም ብሔራዊ የፕላን ኮሚሽን እና የማእከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ከዩ.ኤን ውሜን ጋር በመተባበር ያዘጋጁትን የስርአተ ጾታ አሀዛዊ መረጃ[2] ሪፖርትም እንዲመለከቱ ይመከራል።

2. National Plan Commission and Central Statistics Agency of Ethiopia, Gender Statstics Report



# ክፍል 2. የሁለተኛው አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (2008-2012) የስርአተ ጾታ እኩልነት ኢላማዎች

የሴቶችን ተጠቃሚነት የተመለከቱ ዒላማዎች በሁለተኛው የዕ.ት.ዕ ፒላሮች ውስጥ የተካተቱ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሚከተሉትን ይጠቀሳሉ

- የሰው ኃብት ልማትና የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ መሠረታዊ አቅጣጫ አንጻር የተቀመጡ ዒላማዎች፡-
- የሴቶችንና የወንዶችን የትምህርት ተሳትፎ ምጣኔ ልዩነትን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት 1ኛ ዕርከን (1-4) በ2007 ከነበረበት 0.93፡1 በ2012 ወደ 0.99፡1፣ የሁለተኛ ደረጃ ሁለተኛ ዕርከንን (11-12) ከ0.85፡1 ወደ 0.92፡1 ማድረስ፤

### በጤና ሴክተር የተቀመጡ ዒላማዎች

- የምግብ ዋስትናን በቤተሰብ ደረጃ የማረጋገጥ፣ የእናቶችና ህፃናት እንክብካቤ፣ የጤና አገልግሎት እንዲዳረስ የማድረግና ጤናማ ከባቢ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ይሆናል፡፡
- የእናቶች ሞት ምጣኔ በ2007 እንደተደረሰበት ከተገመተው 420/100000 በ2012 ወደ 199/100000 ዝቅ እንዲል ማድረግ፤
- ከ5 ዓመት በታች ያሉ የህጻናት ሞት በ2007 ከነበረበት 64/1000 ወደ 30/1000 ማውረድ፤
- ዕድሜያቸዉ ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ሞት ምጣኔ ከ44/1000 ወደ 20/1000 ለማውረድ ዕቅድ ተይዟል፡፡
- የወሊድ መቆጣጠሪያን በ2007 ከተደረሰበት 42 በመቶ ወደ 55 በመቶ ለማድረስ ታቅዷል፡፡

## በግብርና ሴክተር ከገጠር መሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የተቀመጡ ዒላማዎች

- በ359 ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ 28.6 ሚሊዮን ማሳዎች ላይ የሁለተኛ ደረጃ ቅየሳና ምዝገባ ሥራ በማካሄድ ለ7.2 ሚሊዮን አባወራዎች/እማወራዎች የመሬት ይዞታ የመጠቀም መብታቸውን የሚያረጋግጥ ሠርተፍኬት መስጠት፤

በሌላ በኩል በፆታ የተለየ አመልካችና ዒላማ ያላስቀመጡ ሴክተሮችም ከተቋቋሙበት ተግባርና ሀላፊነት አንጻር የሴቶችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት የሚያረጋግጡ አመልካችና ኢላማዎችን በመቅረጽ እየሰሩ መሆናቸውን ክትትል ማድረግና ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በሁለተኛው አምስት ዓመት የዕትዕ እንደ አንድ መሰረታዊ አቅጣጫ የተቀመጠው የሴቶችንና የወጣቶችን ብቃት፣ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ ነው፡፡ ዓላማውም፡-

> “የሴቶችንና ወጣቶችን ሁለንተናዊ ብቃት በመገንባት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፣ በሀገሪቱ ልማት ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች በመፍጠር የራሳቸውን ሚና እንዲያበረክቱ ማስቻል” ነው፡፡

የሁለተኛው አምስት አመት የዕትዕ የሚከተሉትን ሶስት የትኩረት መስኮች አስቀምጧል፡፡

1. የሴቶችንና የወጣቶችን አደረጃጀቶች ማጠናከር፣
2. በነዚህ አደረጃጀቶች አማካኝነት ሴቶችና ወጣቶች በአገሪቱ የልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ በመሳተፍ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣
3. አደረጃጀቶቹ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡

## እቅዱ ከሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት አንጻር የሚከተሉትን ዒላማዎች አስቀምጧል

- የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ከማሳደግ አንጻር 4.13 ሚሊዮን ሴቶች በጥቃቅንና አነስተኛ፣ 2.6 ሚሊዮን በራስ አገዝ፣ 5 ሚሊዮን በህብረት ስራ ማህበራት ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

- 6.2 ሚሊዮን ሴቶች የቁጠባ ባህላቸውን እንዲያሳድጉ በማድረግ 8.1 ቢሊዮን እንዲቆጥቡ የሚደረግ ሲሆን 2.24 ሚሊዮን ሴቶች 8.04 ቢሊዮን የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ ሁኔታዎች እንዲመቻችላቸው ማድረግ፤

- በአጠቃላይ ሴቶችን በጥ/አ/ኢ ልማት ዘርፍ ያላቸውን ድርሻ አሁን ከሚገኝበት ከ41.47 በመቶ በ2012 ወደ 50 በመቶ ማሳደግ፤

- በግብርና ዘርፍ የሴቶችን ተጠቃሚነት በተመለከተ 10.1 ሚሊዮን ሴቶች በግብርና፣ 1.5 ሚሊዮን ከግብርና ውጭ ባሉ የስራ መስኮች እንዲሰማሩ በማድረግ በአሁኑ ወቅት 27 በመቶ የሆነውን ወደ 50 በመቶ ለማሳደግ ግብ የተጣለ ሲሆን በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም እማወራዎች የመሬት ተጠቃሚነት መብታቸዉን ማረጋገጥ እንዲሁም 5.8 ሚሊዮን ሴቶች የተስማሚ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በአየር ንብረት ለውጥ ተጎጂ በሆኑ 30 ወረዳዎች የሚገኙ 36000 ተጋላጭ ሴቶች ስልጠና በመስጠት በግብርናና በአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል

- በኢኮኖሚ እጥረት ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለ55000 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሴት ተማሪዎችና ለ50 የሴት ተማሪዎች ማህበራት የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ የፋይናንስ እና የማቴሪያል ድጋፍ ይደረጋል፣ በተለያዩ ክልሎች የተገነቡ 10 ሆስቴሎችን በቁሳቁስ የማጠናከር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

- የሴቶችን ውሳኔ ሰጭነት ከማሳደግ አንጻር ሴቶች በህግ አውጪ በ2007 ከነበረበት 38 በመቶ በ2012 ወደ 50 በመቶ፣ በአስፈፃሚ አካላት የፖለቲካ አመራር በ2007 ከነበረበት 9.2 በመቶ በ2012 ወደ 30 በመቶ እና በህግ ተርጓሚ በ2007 ከነበረበት 20.6 በመቶ በ2012 ወደ 35 በመቶ ለማድረስ ግብ ተጥሏል፡፡

- የምርትና ገበያ ቦታ አቅርቦትን በተመለከተ 1.6 ሚሊዮን ለሚሆኑ ሴቶች የገበያ ትስስር ለመፍጠርና 1.5 ሚሊየን ለሚሆኑ ሴቶች የመሸጫ ቦታ እንዲመቻችላቸው ለማድረግ የታቀደ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ አንድ የገበያ ማዕከል በመገንባት ሴቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡



# ክፍል 3. የስርአተ ጾታ ጉዳይ እና ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ዝምድና

የስርአተ ጾታ ጉዳይ በማህበረሰቡ ውስጥ ከሴቶችና ወንዶች ህይወትና ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች ማለትም በሀብት ተደራሽነት፣ ሀብትን በመጠቀም፣ በተግባርና ሀላፊነቶቻቸው እንዲሁም ከለውጥ ስራዎችና ከፖሊሲዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ በሴቶችና ወንዶች መካከል ያለ ልዩነት ማለት ነው።

በጥቅሉ የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በሴቶች እና በወንዶች መካከል ያለ የተግባር እና የግንኙነት ልዩነት ማለት ሲሆን በግለሰብ ወይም በቡድን ደረጃ እኩል ያልሆነ ወይም በተለየ ሁኔታ መታየትን ሊያስከትል የሚችል ነው። በብዛት የተለመዱት የስርአተ ጾታ ጉዳዮች ከሀብት ተደራሽነትና ተጠቃሚነት፣ ከእድሎች ወይም ከውሳኔ ሰጭነት አንጻር ከሚፈጠሩ ኢ-ፍትሀዊነት ጋር በተያየዘ ነው።

የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና በአገር ደረጃ ከማህበረሰቡ የማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና የፖለቲካ ስርአት ጋር የተያያዙ ናቸው። በመሆኑም የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በተለያዩ አገሮች፣ ክልሎች እና ሴክተሮች እንዲሁም በአንድ ክልል ውስጥ ባሉ ማህበረሰቦች መካከል የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

## የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በልማት ላይ ያላቸው ተጽእኖ

ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ሴቶች ከሀብቶች፣ ከጥቅማጥቅምና ከተለያዩ እድሎች ያላቸው ተጠቃሚነት ከወንዶቹ አንጻር አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር በውሳኔ ሰጭነትም ረገድ ያላቸው ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ የሚያስብል ነው። በዚህ የተነሳም በከፋ ድህነት ውስጥ የሚገኙና በተጨማሪም ለዚሁ ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች በርካታ ናቸው። በሌላ በኩል እነዚህ የስርአተ ጾታ ጉዳዮች ለአገር ልማት በተቀረጹ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም እነዚህን ለማስፈጸም በሚመደበው ሀብት ግምት ውስጥ ካልገቡ የተቀረጹት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ከስርአተ ጾታ አንጻር ያልተፈለገ ውጤት ሊያስከትሉና የታለመውን ግብ ላያሳኩ ይችላሉ።

## የስርአተ ጾታ ጉዳዮች እና ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት ያላቸው ግንኙነት

የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙለትን ተልእኮ ሙሉ በሙሉ ማሳካት የሚችሉት ሴቶችና ወንዶችን እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ ሲያደርጉ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ በቅድሚያ ሴክተሩ ከሚሰጠው አገልግሎት ወይም ምርት አንጻር በሴቶችና ወንዶች መካከል ያለው የተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ክፍተት/ልዩነትን መለየት በጣም አስፈላጊ ነው። እነዚህን ልዩነቶች መለየት የሚቻለው በጾታ እና በስርአተ ጾታ የተለዩ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን መረጃዎቹ የሚያሳዩትን ልዩነቶች በመገምገም ነው። ይህም ሴክተሩ ከሚሰጠው አገልግሎት ወይም ምርት ወይም እድሎች አንጻር በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለውን ልዩነት የተጠቃሚነት እና ተሳታፊነት ልዩነት የ(ሴክተሩን የስርአተ ጾታ ጉዳዮች) የሚያሳይ ይሆናል ማለት ነው።

ተቋማቱ እነዚህን የሴክተሩን የስርአተ ጾታ ጉዳዮች ከለዩ በኋላ እነዚህን ጉዳዮች ለመፍታት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይቀርጻሉ። እነዚህን እርምጃዎች ተግባራዊ ለማድረግም በጀት ዋነኛው መሳሪያ ነው። በዚህ መሰረት ለስርአተ ጾታ በጀት መሰረት ለመጣል ከሚያስፈልጉ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ የስርአተ ጾታ ጉዳዮችን በአግባቡ መለየት ይሆናል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን ሶስት ደረጃዎች በመጠቀም ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል።

**1.** ቁልፍ የስርአተ ጾታ ጉዳዮችን መለየት

በየሴክተሩ የሚታዩ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን ከሴክተሩ ባህሪይ አንጻር ለምሳሌ በግብርናው ዘርፍ የመሬት ባለቤትነትና የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ፣ የግብርና ትምህርትና ስልጠና፣ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የግብርና ግብአቶች አቅርቦት እና የግብርና ገበያ እንዲሁም ቴክኖሎጂ ማፈላለግ ጋር በተያየዘ የሚነሱትን የስርአተ ጾታ ጉዳዮች መለየት፣

**2.** የስርአተ ጾታ ጉዳዮች መንስኤዎችን መለየት

የስርአተ ጾታ ጉዳዮች መንስኤዎቹ ለጉዳዮቹ ቀጥተኛ/የቅርብ፣ ቀጥተኛ ያልሆነ እና ዋና ምንጮች/መነሻ ምክንያቶች በቅደም ተከተል ሊቀመጡ ይችላሉ።

ቀጥተኛ/የቅርብ መነሻ ምክንያት፡ በቀጥታ ለችግሩ አስተዋጽኦ ያደረገው ምክንያት፤ ለምሳሌ የጤና ተቋማት በአቅራቢያ አለመኖር ሴቶች በጤና ተቋማት እንዳይወልዱ ያደርጋቸዋል።

ቀጥተኛ ያልሆነ መነሻ ምክንያት፡ በተዘዋዋሪ መንገድ ለችግሩ አስተዋጽኦ ያደረገው ምክንያት፤ ሴቶች በጤና ተቋማት እንዲወልዱ ወንድ የትዳር አጋሮች የሚያደርጉት ድጋፍ ዝቅተኛ መሆን፤

ዋና ምክንያት፡ ለችግሩ እንደ ዋና ምክንያት የሚነሳ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ እንደ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት፣ ፖሊሲዎች፣ አመለካከቶች፣ ስሜቶች፣ ባህሪዎች፣ ልማዶች፣ ሀይማኖቶች እና ጎጂ እምነቶች ያሉ ምክንያቶች ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ማህበረሰቡ ሴቶች በጤና ተቋማት ሲገላገሉ ያለውን ጥቅም በአግባቡ አለመረዳት፣ የአስተሳሰብ ችግር መኖር፣ ወዘተ.

**3.** ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ መፍትሄዎች

ይህ በዋናነት ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች መንስኤ ለሆኑት ችግሮች መፍትሄ የሚሆኑ እርምጃዎችን መለየትና ተግባራዊ ማድረግን ያጠቃልላል። ለምሳሌ ከዚህ በታች የሚገኘውን ሰንጠረዥ በመመልከት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ሶስቱን ደረጃዎች በመጠቀም በቀላሉ እንዴት ተግራዊ ማድረግ እንደሚቻል መመልከት ይቻላል።

| የስርአተ ጾታ ጉዳዮች | ምክንያቶች/መንስኤዎች | መፍትሄዎች/ተግባራት |
|---|---|---|
| የልጃገረዶች ከፍተኛ የትምህርት ማቋረጥ ምጣኔ | በአቅራቢአቸው ት/ቤት አለመኖር<br><br>በልጃገረዶች ትምህርት ላይ የማህበረሰቡ አመለካከት | በየቀበሌው አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን መገንባት<br><br>በልጃገረዶች ትምህርት ላይ የማህበረሰቡን አስተሳሰብ የሚቀይሩ ሥራዎችን/ንቅናቄዎች/ሥልጠናዎችን ማዘጋጀት |
| በአመራር/የውሳኔ ሰጪነት ቦታዎች የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን | ሴቶች በአመራርነት  ላይ እንዳይሳተፉ የሚያደርጉ ልማዶችና ማጥላላቶች<br><br>ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት | ለሴቶች ትምህርትን/ስልጠናን ማዘጋጀት<br><br>አርአያ የሚሆኑ ሴት አመራሮችን ማስተዋወቅ |
| በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የሴት ባለሀብቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን | በዘርፉ ያሉ ማበረታቻዎች እና አጠቃላይ ስለዘርፉ ያሉ መረጃዎች ለሴቶች ተደራሽ ያለመሆን | ሴት ባለሀብቶች በዘርፉ ተሳትፎአቸው እንዲጨምር ማበረታቻዎችነ በመቅረጽ መተግበር<br><br>መረጃዎችን ለሴቶች ተደራሽ ማደረግ |

የም/ቤቱ አባላት የክትትልና የቁጥጥር ሚናቸውን በመጠቀም ለእያንዳንዱ ሴክተር ፖሊሲ መሳካት አስፈላጊ ለሆኑ የስርአተ ጾታ ጉዳዮች ሴክተሩ ምላሽ እንዲሰጥ በማድረግ እና በየሴክተሩ በጀት የስርአተ ጾታ ተኮር በጀት ሴክተሩ መመደቡን በማረጋገጥ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራር ትግበራ ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡ ም/ቤቱ ከላይ የተገለጹትን ሶስት ደረጃዎችንም በመጠቀም የመንግስት ተቋማት/ሴክተሮች ተግባራቸውን ስለማከናወናቸው ሪፖርት መጠየቅም ይችላል፡፡ ሌላው የም/ቤቱ ተግባር እነዚህን የስርአተ ጾታ ጉዳዮችን ረቂቅ የተደረገ በጀት ለም/ቤቱ በሚቀርብበትና ውይይት በሚደረግበት ወቅት በማንሳት ትኩረት እንዲያገኝ ማድረግ ይቻላል፡፡ ለዚህም አጋዥ የሚሆኑ የተመረጡ ሴክተሮች ዝርዝር የስርአተ ጾታ ጉዳዮችና መፍትሄዎቻቸው በአዝል 3 ላይ ቀርበዋል፡፡ የም/ቤቱ አባላት እነዚህን ዝርዝር የስርአተ ጾታ ጉዳዮች በማንሳት እንዲሁም የቀረቡትን አማራጭ መፍትሄዎች በበጀት ውይይት እንዲሁም በክትትልና ቁጥጥር ወቅት በማንሳትና ምላሽ በመሻት ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ፡፡



# ክፍል 4. የምክር ቤቱ አባላት በጀትን ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ምላሽ ሰጪ ከማድረግ አንጻር እንዴት አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ?

እንደሚታወቀው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራሉ መንግስት ከፍተኛ የስልጣን ባለቤት ሲሆን የሀገሪቱን ህግ የማውጣት፣ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን የማጽደቅ፣ ዓለም አቀፍ ሥምምነቶችን መርምሮ የማጽደቅ፣ የፌዴራሉን መንግሥት በጀት የማጽደቅ እና አስፈጻሚ አካላትን የመከታተል እና የመቆጣጠር ስልጣንና ኃላፊነት ያለው ነው።

ስለሆነም እነዚህ የም/ቤቱ ስልጣንና ኃላፊነቶች ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻርም ከፍተኛ ፋይዳ ያለው ሲሆን፣ በዚህ ክፍል የም/ቤቱ አባላት ይህን ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የሚያግዝ መሣሪያ ቀርቧል።

## 4.1 የበጀት አዘገጃጀት፣ የማጽደቅ እና አተገባበሩን የመከታተልና የመቆጣጠር ሂደት እንዴት ይከናወናል?

በኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 1 የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የሀገሪቱ ትልቁ ሥልጣን ያላው አካል እንደሆነ ይገልጻል። በዚህም መሠረት በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 10 እና 11 ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ኃላፊነቶች ውስጥ የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንዲሁም የፊስካልና የገንዘብ ፖሊሲዎችን ማጽደቅ በአብነት የሚጠቀሱት ናቸው። በተጨማሪም ታክስና ቀረጥን የመጣል እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት በጀት የማጽደቅ ሥልጣን ያለው አካል ነው። በዚህም መሰረት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 648/2001 አንቀጽ 18 ላይ እንደተቀመጠው የእያንዳንዱ የበጀት ዓመት የፌዴራል መንግሥት ገቢ፣ ወጪና ለክልሎች የሚሰጠው የበጀት ድጋፍ እንዲሁም ወጪውን አሸፋፈን የሚያሳይ ሲሆን፣ በተሻሻለው አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 970/2008" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣ በአዋጁ ከአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ (2) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (3) ተጨምሯል፤ "የመንግሥት በጀት ዝግጅት ሥርዓተ ጾታን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።" ይላል።

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 970/2008 የተሻሻለዉ እና 648/2001 አንቀጽ 19 እና 20 የገንዘብ ሚኒስቴር የማክሮኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ማቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡ ፡ ማዕቀፉም በዋናነት በዓመቱ ሊሰበሰብ የሚችል አጠቃላይ ገቢ፣ ለመንግሥት መ/ቤቶች ወጪ ሊደረግ የሚችለውን ገንዘብ ግምት በመደበኛና ካፒታል ወጪ በመለየት፣ መደበኛና ካፒታል ወጪዎችን በክፍላተ-ኢኮኖሚ በመለየት፣ በክልል መንግሥታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍ፣ ወጪ አሸፋፈኑንና የቅርብ ጊዜ የማክሮኢኮኖሚ አፈጻጸሞችን ባካተተ መልኩ ተዘጋጅቶ መቅረብ እንዳለበት ያስቀምጣል። ከዚህም በተጨማሪ በማዕቀፉ ውስጥ ዋና ዋና ሆኑ የማክሮኢኮኖሚ ዕቅዶችም መካተት እንዳለባቸው የሚገልጽ ሲሆን፣ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የዓመታዊ በጀት አዘገጃጀትና አቀራረብ ሥርዓት እንዲሁም ለእንያንዳንዱ የበጀት ጥያቄ መሠረት ሊሆን የሚገባውን ከፍተኛውን የወጪ በጀት መጠን ይወስናል።

ከዚህ በመቀጠል የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ለእንዳንዱ ባለበጀት መሥሪያ ቤት የበጀት ጣሪያ በማዘጋጀት የበጀት ጥሪ የሚያስተላልፍ ሲሆን፣ መ/ቤቶቹም ዓመታዊ የበጀት ዕቅዳቸውን በማዘጋጀት ያቀርባሉ፡፡

በመቀጠልም የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስትሩ ለተከታዩ የበጀት ዓመት የሚያስፈልገውን በጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ከዚያም በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በመገኘት በሚኒስትሮች ም/ቤት ተደግፎ ስለቀረበው በጀት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በዚሁ አዋጅ መሰረት በየዓመቱ በጀት እስከ ሰኔ 30 ቀን በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ጸድቆ ሁሉም ባለበጀት መ/ቤቶችና የክልል መንግስታት እስከ ሐምሌ 7 ቀን እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡ ከዚህ በጀትን የማጽደቅ ሂደት ጋር በተያያዘ የም/ቤቱ አባላት በጀትን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር እንዴት እንደሚገመግሙ በዚህ ሰነድ በንኡስ-ክፍል 4.2 ላይ ተቀምጧል፡፡

በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 17 እና 18 መሠረት ምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ሌሎች የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶችን ኃላፊዎች በመጥራት ኃላፊነታቸውን እንዴት እየተወጡ እንዳሉ የመጠየቅ ስልጣንም አለው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ም/ቤቱ የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ክትትል የሚያደርግባቸው ዋና ዋና ዓላማዎች፡-

- የመንግሥት ሀብትና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉ፣
- የተከናወኑ ተግባራት ህግንና ደንብን በተከተለ መንገድ ስለመሆኑ፣
- ፈጣንና ፍትሃዊ የልማት አቅጣጫ ስለመኖሩ፣
- ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ስለመረጋገጡ፣ የዜጎች መብት፣ ሰላምና ደህንነት ስለመረጋገጡ እና
- በመንግስት አካላት መካከል ቅንጅት ስለመኖሩ ለማረጋገጥ ነው፡፡

የማንኛውም የፌዴራል መንግሥት አስፈጻሚ መ/ቤት በተያዘለት ጊዜ ሪፖርቱን ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ በዚህም መሰረት የቋሚ ኮሚቴው ሪፖርቱን ካዳመጠ በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ የህዝብ አስተያየት ለመስማት ጥሪ ያደርጋል፡፡ የሚመለከተው አስፈጻሚ መ/ቤት ሪፖርቱን በቋሚ ኮሚቴው አማካይነት ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ ምክር ቤቱ ሪፖርቱን ካዳመጠ በኋላ ሪፖርቱ ላይ መሠረታዊ ችግር ያለበት መሆኑን ካመነበት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡ የም/ቤቱ አባላት የፌዴራል መንግስት አካላትን በመከታተል እና በመቆጣጠር ስራቸው የስርአተ ጾታ እይታን እንዴት ማካተት እንደሚችሉ በዚሁ ሰነድ በንኡስ ክፍል 4.4 ላይ ተመልክቷል፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 970/2008 (የተሻሻለው) እና 648/2001 አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት እያንዳንዱ ተመርማሪ መ/ቤት ያለፈው ዓመት የሂሳብ ምርመራ ሪፖርቱ በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ከዘመኑ ከሥራ አፈጻጸም ሪፖርቱ ጋር በማቀናጀት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ማቅረብ እንዳለበት ያስቀምጣል፡ ፡ የፌዴራሉ ዋና ኦዲተር የፌዴራል ሚኒስቴር መ/ቤቶችና ሌሎች ኤጀንሲዎችን የሂሳብ ሰነድ በመመርመር የወጣው ወጪ አስቀድሞ በታቀደው መሠረት ስለመሆኑና ለታለመለት ተግባር ስለመዋሉ ኦዲት በማድረግ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ሪፖርቱን ማቅረብ እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ ከዚሁ ኦዲት ግኝት ጋር በተያያዘ የም/ቤቱ አባላት ከሥርዓተ-ፆታ ዕይታ አንጻር ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በዚሁ ሰነድ በንኡስ ክፍል 4.3 ላይ ቀርቧል፡፡

## 4.2 በጀትን በማጽደቅ ሂደት የምክቤቱ አባላት በጀትን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር እንዴት መገምገም ይችላሉ?

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፌዴራል መንግሥትን በጀት መርምሮ የማጽደቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ የፌዴራል መንግስቱ በጀት በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከመጽደቁ በፊት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚኒስተሮች ም/ቤት ተደግፎ በቀረበው በጀት ዙሪያ ዝርዝር መግለጫ አዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያቀርባል፡፡ ረቂቅ የተደገፈውን ዓመታዊ እንዲሁም ተጨማሪ በጀት የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዝርዝር መርምሮ አስተያየቶችን በመጨመር ለም/ቤቱ የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በእነዚህ በህግ በተደነገጉ ሥልጣንና ኃላፊነቶች ምክንያት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ለመተግበር በጀትን የማጽደቅ ሂደቱ እንደ አንድ መግቢያ ነጥብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ሲሆን፣ የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ ተግባራዊ ማድረግ ይቻላል፡፡

### 4.2.1 የበጀት መግለጫ

የበጀት መግለጫ ረቂቅ የተደገፈ በጀት ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሚቀርብበት ጊዜ በገንዘብ ሚኒስቴር አማካይነት የሚቀርብ ሲሆን፣ በዋናነት በአጠቃላይ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በመዳሰስ የመንግሥት አቅጣጫ በአጭሩ የሚቀርብበት ነው፡፡ በዚህም የም/ቤቱ አባላት የሚከተሉትን ማገናዘቢያዎችን በመጠቀም የበጀት መግለጫው ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ በሚሰጥ መልኩ ስለመዘጋጀቱና በአጠቃላይ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መስፈን የመንግሥት ቁርጠኝነትን እንዲረጋገጥ ማድረግ ይችላሉ፡፡

የገንዘብ ሚኒስቴር የበጀት መግለጫውን ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በሚያቀርቡበት ጊዜ የሚከተሉትን ነጥቦች በማንሳት በመግለጫው የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች በምን ዓይነት መልኩ እንደታዩ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

- የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትና የሴቶች መብት መረጋገጥ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ጉዳዮች ውስጥ ስለመሆኑ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከማስፈን አንጻር ስለተያዘው ግብ፣
- የተለያዩ ሴክተሮች በተለይም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከማስፈን አንጻር ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ እንደ ትምህርር፣ ጤና፣ ግብርና፣ ዉሃ ወዘተ. የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መዛባትን ለማስወደግ ያስቀመጡት አቅጣጫን በተመለከተ፣
- በየሴክተሩ ከሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አንጻር ቅድሚያ የተሰጣቸውን ጉዳዮች እንዲገልጹ በመጠየቅ፣
- በየሴክተሩ ከስርአተ ጾታ አንጻር የተቀረጹ ስትራቴጂክ ኢላማዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች እንዲገልጹ በመጠየቅ፤
- በየሴክተሩ የስርአተ ጾታ ጉዳዮችን እልባት ለመስጠት የተቀረጹ ፕሮግራሞች እና ሀብቶችን እንዲገልጹ በመጠየቅ፤
- ቀደም ያለው ዓመት አፈጻጸም ሲቀርብ ከሥርዓተ-ፆታ እኩልነት አንጻር የተገኙ ውጤቶችን እና በጥቅም

ላይ የዋለውን ሀብት ጭምር በግልጽ እንዲቀመጥ በመጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡

ለአብነትም እ.ኤ.አ በ2008/09 የሞሪሼስ ገንዘብ ሚኒስትር የበጀት መግለጫውን ሥርዓተ-ፆታን ባገናዘበ መልኩ ያቀረበ ሲሆን፣ በበጀት አመዳደቡ ላይ የሚከተሉትን ጉዳዮች ትኩረት እንደ ተሰጠባቸው አስቀምጧል

የሴቶችን ስራ አጥነትን ለመቀነስ ፕሮግራም እንደተቀረጸና በዚህም 75 በመቶ ሥራ አጥ ሴቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ፤

ሴቶች የሚያጋጥሟቸውን የብድር አቅርቦት ለመቅረፍ አዳዲስ የብድር አቅርቦት ዘዴን በመጠቀም ብድር ፈላጊ ሴቶች ሙሉ በሙሉ የብድር ተጠቃሚ እንደሚሆኑ፣

ከጋብቻ ጋር ተያያዥ በሆኑ የህግ ችግሮች ምክንያት የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ለሚያጋጥሟቸው ሴት ስራ ፈጣሪዎች ያለ መያዣ የሚቀርበውን የብድር መጠንን ወደ 100,000 አገሪቱ ገንዘብ ከፍ እንዲል እንደሚደረግ ያስቀምጣል፡፡

### 4.2.2 የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የፌዴራሉን መንግሥት ረቂቅ የተደገፈ ዓመታዊና ተጨማሪ በጀትን በጥልቀት የመመርመር አስተያየቱን ለም/ቤቱ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም ይህ ቋሚ ኮሚቴ ረቂቅ በጀቱን በሚገመግምበት ጊዜ በጀቱ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ መሆን አለመሆኑን የሶስቱ የወጪ ምድቦች ስልት እና አምስቱ ደረጃዎች ስልትን አቀናጅቶ በመጠቀም መመርመር ይችላል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን

ማገናዘቢያዎችን በመጠቀም የዕቅድና የበጀት ሂደቱ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ መሆን አለመሆኑን መገምገም ይቻላል፡፡

ሴቶችና ወንዶች ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታ በመተንተን በሴክተር ደረጃ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ተለይተዋል ወይ? ከሆነስ በሴክተሩ በጀት ግምት ውስጥ የገቡት የትኞቹ የስርአተ ጾታ ጉዳዮች ናቸው? የሴቶችንና የወንዶችን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳይ በጾታና በስርአተ ጾታ የተለየና የተተነተነ መረጃ አለ? ለምሳሌ ይህ ማለት በወሊድ የሚሞቱ ሴቶች ቁጥር/ሁኔታ፣ ጨቅላ ህጻናት ሞት ምጣኔ፣ የተማሩ ሰዎች ምጣኔ እንዲሁም ስርአተ ጾታ ተኮር አገልግሎቶች አሰጣጥ የተገልጋዮች አስተያየቶች የመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡

የባለበጀት መ/ቤቶቹ ፖሊሲዎች ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የፖሊሲ ትንተናን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ያደርጋሉ ወይ? ካልሆነ ለምን? ከሆነ ደግሞ ፖሊሲዎቹ በነባራዊ ሁኔታ ትንተና ወቅት ለተለዩ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ የሰጡ ናቸው? ለዋና ዋና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች በአግባቡ ምላሽ የሚሰጡ ፖሊሲዎች አሉ?

ይህ ከሆነ ፖሊሲዎቹ ለተለዩት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች በጥሩ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠትና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት በቂ ናቸው?

የሚሰሩ ስራዎችስ በአግባቡ ተለይተዋል ወይ? ስራዎቹ የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶች ወይስ የአንዱን ጾታ ፍላጎት ብቻ ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው?

በሌላ በኩል ፖሊሲዎቹ እና ፖሊሲዎቹን ለመተግበር የሚቀረጹ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ ያህል እንደ የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም) የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን ያገናዘቡ ከሆኑ ለተፈጻሚነታቸው በቂ የሆነ ሀብት መመደብ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የሚከተሉት ማገናዘቢያዎች የበጀት ምደባን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ለመፈተሽ መጠቀም ይቻላል።

ቀደም ባለዉ ዓመት የሥርዓተ-ፆታ በጀት ትንተና በአግባቡ ተከናውኗል ወይ? በዚሁ መሰረት ግኝቱ በዚህ ዓመት በጀት ዝግጅት ወቅት እንደ ግብዓት ተጠቅመዋል?

በበጀት ሠነዱ ላይ የተቀመጡ ዒላማዎች በፆታ የተለዩ ናቸው?

ሥርዓተ-ፆታን ያገናዘቡ መለኪያዎች ተቀምጠዋል ወይ?

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ናቸው ተብለው ለተለዩት ፖሊሲዎች እና ፖሊሲዎቹን ለመተግበር የሚቀረጹ ፕሮግራሞች በጀት ተመድቧል?

የተመደበው በጀት የተለዩትን የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት በቂ ነው?

የበጀት ምደባው በተለየ ሁኔታ ሴቶችን ወይም ወንዶችን ዒላማ ያደረገ ነው? ከሆነ በምን ምክንያት? በዚህ ዓይነት አሰራር እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው በኡጋንዳ ለሴት ተማሪዎች መጸዳጃ ቤት ግንባታ የሚመደብ በጀት እንዲሁም በተለየ ለሴቶች አነስተኛ ብድር ለመስጠት የሚመደብ ገንዘብ ሴቶችን ብቻ ዒላማ ባደረገ መልኩ ሀብትን የመመደብ አሰራር ነው።

ተቋማቱ ለሰራተኞቻቸው እኩል የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚመድቡት በጀት አለ (ለምሳሌ ለሰራተኞቻቸው ህጻናት የማቆያ አገልግሎት ለመስጠት፣ የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ ክፍያ ጋር ወይም የተለየ ስልጠና ለሴት ሰራተኞች ለማዘጋጀት)? ከተመደበ ለምን አገልግሎት ነው የተመደበው? ካልተመደበ ለምን?

ተቋማቱ ለሴት ሰራተኞቻቸው ለውሳኔ ሰጭነትና አመራርነት የሚያበቃ ልዩ የትምህርና ስልጠና ፕሮግራም የተመደበ በጀት አለ? ከሌለ ለምን ? ወደፊትስ ምን የታቀደ አለ?

የባለበጀት መ/ቤቶቹ ምርትና አገልግሎታቸውን ለማህበረሰቡ ለማቅረብ የሚመድቡት በጀት በአጠቃላይ የሴቶችንና ወንዶችን ልዩ ፍላጎት፣ ያሉበትን ሁኔታ ወዘተ ያገናዘበ ነው ወይ ከተመደበው ወጭ ሴቶችና ወንዶች ተጠቃሚ የሚሆኑት ወይም ተጎጂ የሚሆኑት እንዴት ነው? ለምሳሌ አጠቃላይ ለትምህርት እና ጤና ዘርፍ የሚመደበው በጀት መጨመር ከሀብታም ሴቶች እና ህጻናት የገንዘብ አቅማቸው አነስተኛ ለሆኑ ሴቶችና ህጻናት አዎንታዊ ተጽእኖ አለው፤

## የበጀት ቅነሳ ሞሽንን መመርመር

በጀት ቅነሳ ሞሽንን የበጀት ቅነሳው በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ በመመርመር የበጀት ቅነሳ ሞሽኑን ከስርአተ ጾታ አንጻር መገምገም ያስፈልጋል፡፡

ለአብነትም በማህበራዊ ዘርፍ የሚደረግ የበጀት ቅነሳ ወይም የአገልግሎት ክፍያ መጨመር በአጠቃላይ ሴቶች ላይ በዋናነት ደግሞ የደሃ ደሀ እና አካል ጉዳተኛ በሆኑ ሴቶች ላይ የተለየ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ለምሳሌ በአገልግሎት ከፍያ መጨመር ምክንያት የትምህርት የአገልግሎት ክፍያ ሲጨምር ሁሉንም ልጆች ለማስተማር አቅማቸው የማይፈቅድ ቤተሰቦች ለትምህርት ማቋረጥ በመጀመሪያ ሰለባ የሚያደርጉት ሴት ልጆችን ነው፡፡ ለምሳሌ በዛምቢያ እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ በትምህርት ላይ የአገልግሎት ክፍያ በመጨመሩ ምክንያት የልጃገረዶች መጠነ-ማቋረጥ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ በኬንያም የትምህርት ቤቶች ክፍያ በሚጨምርበት ጊዜ የልጃገረዶች መጠነ-ማቋረጥ ከወንዶች በእጥፍ በልጦ ተገኝቷል፡፡ በሌላ መልኩ በመንግሥት የጤና ተቋማት የሚገኘውን ገቢ ለመጨመር የሚጨመረው የአገልግሎት ክፍያ በሴቶቹ ላይ ከባድ የስራ ጫና ሊፈጥርባቸው ይችላል፡፡ የዚህም ምክንያቱ በአብዛኛው ማህበረሰብ የታመሙ ሰዎችን የማስታመም ኃላፊነት የሴቶች በመሆኑ በጤና ተቋማቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች በአገልግሎት ከፍያ መጨመር ምክንያት ውድ ስለሚሆኑ ታማሚዎች ሳይሻላቸው ከጤና ተቋማቱ ወጥተው ወደ ቤታቸው ስለሚሄዱ ነው፡፡ በተጨማሪም ሴቶቹ ለታመሙ ዘመዶቻቸው ባህላዊ መድሃኒቶችን ፍለጋ የተለያዩ ቦታዎችን በመሄድ ጊዜያቸውን ሊያጠፉ ይችላሉ፡፡

### 4.2.3 የህዝብ አስተያየት ማዳመጥ

በተዘጋጀው ረቂቅ ህግ ወይም ፖሊሲ ዙሪያ የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የህዝብ አስተያየት በሚሰበስብበት ጊዜ ከሥርዓተ-ፆታ ጋር በተያያዘ በተለይም የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶችንና ቅድሚያ የሚሰጡዋቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለበት ሲሆን፣ የሚከተሉትን አካላት በውይይቱ ላይ እዲሳተፉ ማድረግ ይችላል፡፡

- በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች፣
- በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ተመራማሪዎች፣ አማካሪዎች፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታት ካልሆኑ ድርጅቶች፣ የልማት አጋሮች፣
- የማህበረሰብ ቡድኖች፣ በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣

7. Millennium Project Task Force on Gender Equality: Taking action: achieving gender equality and empowering women, 2005.
8. የተሻሻለው ፌዴራሉን ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## 4.3 የም/ቤቱ አባላት ከሥርዓተ-ፆታ ዕይታ አንጻር የኦዲት ግኝትን በተመለከተ ምን ማድረግ ይችላሉ?

የተሸሻለው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ 982/2008 አንቀጽ 4 /2/ ላይ እንደተቀመጠው መሥሪያ ቤቱ የፌዴራል መንግሥትን ሁሉንም ሀብትና ገንዘብ በህጉና በደንቡ መሠረት በአግባቡ መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና ሥራ ላይ መዋሉን የማረጋገጥና ውጤቱን ም/ቤት ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት።

የኦዲት ግኝቱን በተመለከተ ም/ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራት ሊያከናውን ይችላል፡-

የኦዲት ሪፖርቱ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን አተገባበር ማንጸባረቁን ማረጋገጥ፣

ከሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አንጻር ቀደም ባለው ዓመት የተሰጠው የኦዲት ማስታወሻ በአግባቡ እርምጃ ስለ መወሰዱ ማረጋገጥ፣

በተጨማሪም የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የፋይናንሻል ኦዲት ብቻ ላይ ሳይሆን የክዋኔ ኦዲት (ፐርፎርማንስ ኦዲቱንም ) ኦዲት በተቀረፁ ህግ፣ ደንብና መመሪያ መሠረትም የሴቶችን ፍትሐዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን መመልከቱ ተገቢ ሲሆን፣ በዚህም መንግሥት ከመደበው በጀት ማን የበለጠ ተጠቃሚ እንደሆነ ወይም ማን ሳይጠቀም እንደቀረ ለመገመት ዕድል ይሰጣል። በተጨማሪም በቀጣዩ አመት በኦዲት ግኝቱ የታዩ ክፍተቶችን በመለየት የስርአተ ጾታ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ የከተተ በጀት እንዲመደብ መሰረት ለመጣል ያስችላል። በዚህም መሰረት የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉትን ማገናዘቢያዎች በመጠቀም የኦዲት ግኝቱን ከሥርዓተ-ፆታ ዕይታ አንጻር መገምገም ይችላል።

በኦዲት ሪፖርቱ ላይ መንግሥት የመደበው ሀብት በአጠቃላይ የሥርዓተ-ፆታ ፍትሃዊነቱን በሚያሰፍን መልኩ ሥራ ላይ ስለመዋሉ የሚገልጽ ነገር አለው? ይህ ማለት መንግሥት የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማስፈን ያወጣውን ፖሊሲዎችንና በዓለም-አቀፍ ደረጃ የተፈረሙ ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ሥራ ላይ የዋለ ሀብት ስለመኖሩ፤ ይህ ደግሞ ሴቶች ላይ ያተኮረ በጀት ምደባ ላይ ትንተና ማድረግ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ለሴክተሩ የተመደበው በጀት ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መስፈን ያለውን ፋይዳ መገምገምን ያጠቃልላል።

ቀደም ያለውን በጀትና የተስተካከለውን በጀት በማነጻጸር ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ከመሆን አንጻር ክፍተቶችንና ለውጦችን በመዳሰስ፣

## 4.4 የም/ቤቱ አባላት የፌዴራል መንግስት አካላትን በመከታተል እና በመቆጣጠር ስራቸው የስርአተ ጾታ እይታን እንዴት ማካተት ይችላሉ?

የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 17 እና 18 የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶችን የመከታተልና አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ኃላፊዎችን በመጥራት መጠየቅና መወያየት እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን መውሰድ እንደሚችል ይደነግጋል። አስፈጻሚ አካላቱ ላይ የሚደረገው ክትትል ዓላማዎች ውስጥ፡-

ሀ. የመንግሥትና የህዝብ ሀብትና ንብረት በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ፣

ለ. የተከናወኑ ተግባራት ህግንና ደንብ በተከተለ መንገድ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ፣

ሐ. የዜጎች መብት ሰላምና ፀጥታ መጠበቁን ለማረጋገጥ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣

በአጠቃላይ የም/ቤቱ አባላት የሚያደርጉት የክትትልና ግብረ-መልስ ተግባራት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ አንድ የመግቢያ ነጥብ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

### 4.4.1 ለም/ቤቱ የሚቀርቡ ሪፖርቶችና የመስክ ግምገማዎች

እያንዳንዱ የፌዴራል መንግስት አካል ለሚመለከተው የም/ቤቱ የቋሚ ኮሚቴ በተመደበለት ጊዜ ሪፖርቶችን ማቅረብ አለበት፡፡ ከዚህ የም/ቤቱ አባላት ሚና አንጻር የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ እንደ ጥሩ የመግቢያ ነጥብ ሊያገለግል የሚችለው ሪፖርቱን ማቅረብ የሚጠበቅበት የአስፈጻሚ መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች መሆናቸው ነው፡፡ ይህ ዓይነት አካሄድ የመንግሥት ኃላፊዎችን ተጠያቂነት የሚያጎለብት በመሆኑ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈንና ሴቶችን ለማብቃት በቁርጠኝነት እንዲሰሩ የሚያነሳሳቸው ሲሆን፣ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በአግባቡ ተካቶ እንዲሰራ ከማድረግ አኳያ ትልቅ

ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ወይም የም/ቤቱ አባላት የሚከተሉትን ማገናዘቢያዎች በመጠቀም ሪፖርቶቹን ወይም የመስክ ምልከታውን ከሥርዓተ-ፆታ ዕይታ አንጻር መገምገም፣ ጥያቄ እና አስተያየት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

የተገኙ ውጤቶች ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለሴቶችና ለወንዶች ተደራሽ ሆነዋል? እንዴትስ ይገለጻል? ምን ያህል ሴቶችና ወንዶች ተጠቃሚ ሆነዋል? የተበጀተው በጀት ለታለመለት ዓላማ ውሏል?

- በባህሪያቸው ከሥርዓተ-ፆታ ጋር ተያያዥነት ያሏቸው ተግባራት ውጤት ለተፈለገው አካል ተደራሽ ሆኗል? እንዴትስ ይገለጻል? ምን ያህል ተጠቃሚ ሆኑ? በጀቱ መጀመሪያ በታቀደው መሰረት ሥራ ላይ ውሏል?

- ባለበጀት መ/ቤቶች የሴቶችን ልዩ ድጋፍ ርምጃ፣ የህጻናት ማቆያ አገልግሎቶችን እንዲሁም ሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን በተመለከተ መንግስት በዓለም አቀፍ ደረጃ የፈረመውን ሥምምነቶች እየተገበሩ ያለው እንዴት ነው? ምን ያህል ሴቶች ከልዩ ድጋፍ አሰራር ተጠቃሚ ሆነዋል?

- ምን ያህል ባለበጀት መ/ቤቶች ለሠራተኞቻቸው እኩል የሥራ እድል ለመፍጠር የሚያስችለውን በጀት መድበዋል (ለምሳሌ ሴቶችን ለማስተማር፣ የህጻናት ማቆያ አገልግሎት ለመስጠት ወዘተ.)? ለዚህ ከተበጀተው በጀት ስንቶች ተጠቃሚ ሆኑ?

- በአጠቃላይ ለሴክተሩ ከተመደበው በጀት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከማስፈንና ሴቶችን ከማብቃት አንጻር ያለው ፋይዳ ምንድነው?

- ከአሰራር እና በጀት ጋር በተያያዘ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ አካቶ ከመስራት አንጻር ያጋጠሟቸው ችግሮች ካሉ ቢጠቀስ፣

- በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ ላይ ከሥርዓተ-ፆታ ጋር በተያያዘ የተቀመጡ ዒላማዎች አፈጻጸም ከሴክተሩ አንጻር በምን ደረጃ እንደሚገኝ ቢጠቀስ፣

- የቀረበው ሪፖርት ወይም መረጃ በጾታ እና በስርአተ ጾታ የተለየና የተተነተነ መሆኑን ማረጋገጥ፣

### 4.4.2 ሪፖርቶቹን ለህዝብ አስተያየት ክፍት ማድረግ

ቋሚ ኮሚቴው ሪፖርቱን ከሰማ በኋላ ለህዝብ ይፋ ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ ኮሚቴውም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የህብረተሰብ ክፍሎችና የመገናኛ ብዙሀን እንዲገኙ ያደርጋል፡፡ የሚመለከተውም አስፈጻሚ መ/ቤት ሀላፊም ሪፖርቱን የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

በዚሁ መሠረት የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርቱን ለህዝብ አስተያየት ክፍት በሚያደርግበት ጊዜ የሚመለከታቸውን አካላት ሁሉ ማለትም በሥርዓተ ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖችን፣ በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ተመራማሪዎችን፣ አማካሪዎችን፣ የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችንና በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በመጋበዝ ሀሳብ/ አስተያየታቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግ ይችላል፡፡

## 4.5 የም/ቤቱ አባላት ህግንና ፖሊሲን በማውጣት ሂደት ከስርአተ ጾታ አንጻር እንዴት መመርመር ይችላሉ?

### 4.5.1 በበጀትና በህጎች መካከል ያለው ግንኙነት

በጀት ህጎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቅም መሳሪያ ነው፡፡ ስለሆነም ህጎችን ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ ማድረግ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ ወሳኝ መሰረት ነው፡፡

### 4.5.2ህግን የማውጣት ሥልጣን

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግሥት አዋጅ አንቀጽ 55 የህዝብ ተወካዮች ም/ቤትን ሥልጣንና ተግባር የሚደነግግ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ም/ቤቱ፡-

- ለፌዴራል መንግስት በተሰጠው የስልጣን ክልል ህጎችን ያወጣል፡፡ አንቀጽ 55 (1)

- ም/ቤቱ የሰራተኛ ጉዳይ ህግ፣ የንግድ ህግ(ኮድ)፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህጎች ያወጣል፡፡ አንቀጽ 55 (3-6)

- የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን፣ የፋይናንስና የገንዘብ ፖሊሲዎች ያጸድቃል፣ ገንዘብን፣ የብሔራዊ ባንክ አስተዳደርን፣ የውጭ ምንዛሪንና ልውውጦችን

በተመለከተ ዝርዝር ህግ ያወጣል፤ አንቀጽ 55 (10)

- የህግ አስፈጻሚው አካል የሚዋዋላቸውን ዓለምአቀፍ ሥምምነቶችን ያጸድቃል፤ አንቀጽ 55 (12)

### 4.5.3 የም/ቤቱ አባላት ህግን ከማውጣታቸው በፊት ከሥርዓተ-ጾታ አንጻር እንዴት መመርመር ይችላሉ?

ህጎች ለሥርዓተ-ጾታ ምላሽ ሰጪ እንዲሆኑ ም/ቤቱ የሚከተሉትን አሰራሮች ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፡፡

ሀ. ለእያንዳንዱ ረቂቅ የፖሊሲ/የበጀት ሠነድ ለም/ቤቱ ከመቅረቡ በፊት የሥርዓተ-ጾታ ትንተና እንዲከናወን በመጠየቅ ወይም እያንዳንዱ ረቂቅ የፖሊሲ/የበጀት ሠነድ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና ስለመደረጉ እንዲረጋገጥ የሚያደርግ ሞሽን ተግባራዊ በማድረግ፤

ለምሳሌ፡ ፊጂ የሚትባል ሀገር ወደ ም/ቤቱ የሚላኩ የበጀት ሠነዶች በሙሉ የሥርዓተ-ጾታ ትንተና እንዲደረግባቸው የሚያስገድድ ህግ አውጥታለች፡፡

ለ. የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ አባላት የውሳኔ ሀሳብ እና አስተያየት በማቅረብ ሚናው እንዲሁም ሌሎችም የም/ቤቱ አባላት በውይይት ወቅት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ይችላሉ፡፡

ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ሲቀረጹ ነባራዊ ሁኔታዎች ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ተተንትነዋል? የሴቶችና የወንዶች ፍላጎቶች እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጧቸው ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ገብተዋል?

ህግ ወይም ፖሊሲ እንዲወጣለት የተፈለገው ጉዳይ (ችግር) በሴቶችና ወንዶች ላይ ተጽእኖ የሚያደርሰው እንዴት ነው? ተመሳሳይ ወይስ የተለያየ ተጽዕኖ ያደርሳል? በሴቶችና በወንዶች ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ የተለያየ ከሆነ፣ የተለያየ ተጽእኖ የሚያደርሰው ለምንድን ነው? ከሥርዓተ-ፆታ ሚና መለያየት ወይስ ከማህበረሰቡ አስተሳሰብ የተነሳ ወይስ ኢ-ፍትሃዊ ከሆነ የሀብት ክፍፍል በመነጨ ወይስ ከፆታዊ ጥቃት ጋር በተያያዘ ምክንያት ነው የተለያየ ተጽእኖ የሚያደርሰው?

አሁን የሚወጣው ህግ ወይም ፖሊሲ በሴቶችንና ወንዶች ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሰው እንዴት ነው? ሴቶች እና ወንዶች ከፖሊሲው ወይም ከህጉ እንዴት ነው ተጠቃሚ የሚሆኑት? ወንዶችንና ሴቶችን እኩል ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል? ፍትሃዊነቱስ? ተግባራቸውን ወይም ለሀብት ያላቸውን ተደራሽነትና ተጠቃሚነት ወይም በኑሮ ሁኔታቸው ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ምንድነው?

በመውጣት ላይ ያለው ህግ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ክፍተትን የሚቀንሰው እንዴት ነው? በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን የእኩልነት መዛባት ለማስተካከል አስተዋፅኦ አለው? የሥርዓተ-ፆታን እኩልነት ለማስፈንና ሴቶችን ለማብቃት ከተቀመጠው አቅጣጫ ጋር የሚስማማ ነው? በሴቶች ላይ የሚፈጸምን ማንኛውም መድሎዎ ለማስወገድ ከተፈረመው ድንጋጌ ጋር የተጣጣመ ነው?

ሐ. የፖሊሲ ቀረጻ ሂደቱ በመረጃ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማረጋገጥ፡-

ፖሊሲው ለም/ቤቱ ሲቀርብ በፖሊሲ ቀረጻ ሂደቱ ምን ዓይነት መረጃ ሥራ ላይ እንደዋለ በተለይም በፆታ የተከፋፈለና ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር የተተነተነ መረጃ ተግባር ላይ መዋሉን የም/ቤቱ አባላት መጠየቅና ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ የዚህ ዓይነት ጥያቄ በም/ቤቱ አባላት በሚነሳበት ጊዜ አስፈጻሚ አካላት ሌሎችንም ተግባራት በሚያከናወኑበት ወቅት በፆታ የተከፋፈለ መረጃ መሰብሰብን እንዲያጤኑት ስለሚያደርጋቸው መረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔዎችን ለማሳተላለፍ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በዚህም መሠረት የም/ቤቱ አባላት በተለይም የሚከተሉትን ነጥቦች አንስተው መጠየቅ ይችላሉ፡-

በጉዳዩ ዙሪያ በፆታ የተከፋፈለ መረጃ ይገኛል? ያለ ከሆነ መረጃው ምን ዓይነት የስርአተ ጾታ ክፍተት ያሳያል?

መረጃው የሌለ ከሆነ ለምን?

ያሉ መረጃዎችስ ወቅታዊነቱን የጠበቁ ናቸው?

መ. የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ማረጋገጥ፡-

ጉዳዩ በዋናነት የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የህዝብ አስተያየት ለመስማት የህዝብ ፎረሞችን ሲያዘጋጅ የሚከተሉት ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማረጋገጥና አስተያየታቸውን መስማት ይችላል፡፡

- በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች
- በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ ተመራማሪዎች፣ አማካሪዎች፣ መንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከልማት አጋሮች
- የማህበረሰብ ቡድኖች፣ በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የሚሰሩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች

## 4.6 የስርአተ ጾታ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶች

የስርአተ ጾታ በጀት በአግባቡ እንዳይተገበር እያጋጠሙ ካሉ ተግዳሮቶች መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡

እና አካተው የሰሩ ደግሞ የሚበረታቱበት አሰራር አለመኖሩ የስርአተ ጾታ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ እያጋጠሙ ካሉ ተግዳሮቶች መካከል መጠቀስ የሚችል ነው።

ሐ. የየሴክተሩን ስርአተ ጾታ ጉዳዮች፣ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ የነባራዊ ሁኔታዎች ጥናት አሰራር፣ ከስርአተ ጾታ ጋር ተያያዥ የህግ ማእቀፎች እና የስርአተ ጾታ በጀት እውቀትና ክህሎት አለመዳበር፡- በእቅድ፣ በበጀትና በትግበራ እንዲሁም በክትትል ስራ ለሚሳተፉ ሰራተኞች በሙሉ የስርአተ ጾታ እውቀትና ክህሎት መኖር አስፈላጊ እንደመሆኑ ተከታታይ የሆኑ ተግባር ተኮር ስልጠናዎች በብዛት አለመሰጠታቸውና በመንግስት ተቋማትም ከሰራተኞች ፍልሰት ጋር በተያያዘ የሰለጠኑት ሲለቁ በምትካቸው ለሚቀጠሩት ቀጣይነት ያለውን የአቅም ግንባታ ስልት አለመተግበሩ ሌላው ተግዳሮት ነው።

መ. በጋራ የመስራት ልምድ አለመዳበር፡- በተቋም ደረጃ በሚደረጉ የክትትልና ግምገማ ስራዎች ወቅት በጋራ የመስራት ልምድ አለመዳበር፣ በዲፓርትመንቶች መካከል በተለይም ከስርአተ-ጾታ ክፍል ጋር በጋራ የመስራት ልምድ አለመዳበር እንዲሁም በክትትል ስራዎች የስርአተ-ጾታ ባለሙያዎችን አለማሳተፍ/ እንዲሳተፉ ሁኔታዎችን ያለመመቻቸት ችግሮች በሰፊው ይስተዋላሉ።

ሠ. መረጃን መሰረት ያደረገ እቅድ አለማቀድ፡- በየዳሬክቶሬቶቹ የስርአተ ጾታ ስራዎችን መረጃን መሰረት አድርጎ ያለማቀድ ችግሮችም በጀቱን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የስርአተ ጾታ ችግሮችና ክፍተቶች እንዳይውል ያደርጋል። በዚህ ረገድ በተለያዩ ተቋማት ችግሮች አሉ።

ረ  የታቀደው እቅድና የተመደበው በጀት ያመጣው ለውጥ አለመገምገሙ

## መፍትሄ

የም/ቤቱ ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች ወጥ በሆነ መልኩ ክትትል የሚያደርጉባቸውን ተቋማት የስርአተ ጾታ እቅድና በጀት አፈጻጸም በመገምገም ተቋማት ተጠያቂ የሚሆኑበትን ባህል መገንባት፤ የተቋማቱ የበላይ ሀላፊዎችም በየተቋማቸው የተጠያቂነት አሰራርን እንዲተገብሩ ማሳሰብ፤ ጥሩ አፈጻጸም ያላቸውን ተቋማትም ማበረታታትና እውቅና መስጠት፤

ተቋማቱ ለሰራተኞቻቸው በስርአተ ጾታ ጉዳዮች እንዲሁም የሴት ሰራተኞችን ልዩ የስልጠና ፍላጎቶችን በሚመለከቱ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው ወጭ ቆጣቢ የሆነ ተግባር ተኮር የግንዛቤ ማስጨበጫ አሰራሮችን እንዲዘረጉ ማሳሰብ፤

ለጋራ አላማ በጋራ የመስራት ልምድን ማጠናከር

ም/ቤቱ ክትትል ከሚያደርግባቸው ተቋማት መካከል የገንዘብ ሚኒስቴር መ/ቤትን እና ስታትስቲክስ ኤጀንሲን የተካተቱ በመሆናቸው ተቋማቱ ተግባራዊ የሚያደርጓቸውን አሰራሮች ከስርአተ ጾታ አንጻር መመርመርም አስፈላጊ ነው።



# ክፍል 5. የማስፈጸሚያ ስልት

በበጀት ሂደት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ዕይታን በተገቢ ሁኔታ ለማንጸባረቅ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት አስቻይ ሁኔታዎች ትኩረት ሊሰጥባቸውና ተግባራዊ ሊሆኑ ያስፈልጋል።

## 5.1 በሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ዙሪያ የም/ቤቱን አባላት ግንዛቤ ማሳደግ

ስለ ሴቶችና ወንዶች የሚኖረን ዕይታ ቅርፅ እየያዘ የሚመጣው ገና ከጨቅላነታችን ጀምሮ ሲሆን፣ ይህን ከማድረግ አንጻር ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ማህበረሰቡ፣ መምህራን፣ መጽሐፍት ወዘተ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ። ስናድግ ደግሞ ይህንን እይታ በእለት ተእለት ኑሮዋችን ተግባራዊ እናደርጋለን። የም/ቤቱ አባላትም የሰፊው ኢትዮጵያ ህዝብ አካል በመሆናቸው በሀገሪቱ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን የሚያዛቡ ሥር የሰደዱ ባህላዊና ሐይማኖታዊ አስተሳሰቦች መሻሻሎችን ቢያሳዩም አሁንም ያልጠፉ በመሆኑ ይህ አስተሳሰብ በእነሱም ላይ ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀሬ ነው። ስለሆነም በአስተሳሰብ ውስጥ ዘልቆ የገባውንና የተዋሀደውን ለሥርዓተ-ፆታ ያለውን የተሳሳተ ዕይታ፣ አመላካከትና እምነት ለማቃናት መስራት ያስፈልጋል።

በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የአስተሳሳብንና የአመለካከትን ለውጥ ለማምጣት ከሚሰጠው የአቅም ግንባት ሥልጠና ባሻገር ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ የቴክኒክ/የክህሎት የአቅም ግንባታ ሥራዎችንም መስራቱ እጅግ ወሳኝ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ከአመለካከት ለውጥ ባለፈ በጀትን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር መገምገም እውቀትና ክህሎትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው። በዚህም የፌዴራሉን መንግሥት በጀት ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ለመገምገም ሁሉም የም/ቤቱ አባላት ቢያንስ መሰረታዊ የሥርዓተ-ፆታ ጽንሰ ሀሳብ፣ ስለ ሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መስፈን ለልማት ያለው ጠቀሜታ፣ ስለ ሥርዓተ-ፆታና በጀት ዝምድና ያላቸውን እውቀት ማዳበር ያስፈልጋል።

የም/ቤቱ የአባላቱን ግንዛቤ የሚያሳድጉ ሥራዎችን ለማከናወን የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ሊያደርጉ ከሚችሉ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት መሥራት ይችላሉ።

## 5.2 በበጀት ዙሪያ የጥናት ውጤቶችንና መረጃዎችን ተደራሽነት ማሳደግ

የበጀትን ውሳኔ ከመደረጉ በፊት የሥርዓተ-ፆታ በጀት ትንተና ማድረጉ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ በመሆኑ የገለልተኛ አካላት የሥርዓተ-ፆታ በጀት ትንተና ጥናቶችና መረጃዎች አስፈላጊ ናቸው። የም/ቤቱ አባላት ትንተናውን የግድ በራሳቸው ማከናወን ላያስፈልጋቸው የሚችል ሲሆን፣ በዋናነትም በአሰራሩ ዙሪያ በቂ እውቀት ያሉአቸው ገለልተኛ ባለሙያዎች የስርአተ ጾታ በጀቱን ተንተነው ለም/ቤቱ አባላት ተደራሽ ማድረግ ይችላሉ። እነዚህም አካላት በትምህርት ተቋማት የሚሰሩ ባለሙያዎች፣ አማካሪዎች፣ በግል ዘርፍ የተሰማሩ ኢኮኖሚስቶች ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌላ በኩል የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ማህበረሰብ አቀፍ ከሆኑ ድርጅቶች ወይም በሴቶች ላይ ከሚሰሩ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በበጀት ምደባ ላይ የሥርዓተ-ፆታ በጀት ትንተና እንዲያደርጉ በመጋበዝ ውጤቱን እንደ አስፈላጊነቱ ሊጠቀመው ይችላል።

እቅድ እና በጀት በሚቀርብበት ጊዜ የም/ቤቱ አባላት በተለይም በፆታና በስርአተ ጾታ የተከፋፈለ መረጃ እንዲቀርብላቸው መጠየቅ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ም/ቤቱ ሁሉንም አስፈጻሚ መ/ቤቶች በዋና ዋና አመላካቾች ላይ በፆታና ስርአተ ጾታ የተከፋፈለ መረጃ በአግባቡ እንዲይዙና በቀጣይ የሚታቀዱ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች እነዚህን በጾታ እና በስርአተ ጾታ የተለዩ መረጃዎች ትንተና ውጤትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን ማድረግ ይችላሉ።

## 5.3 የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ ማካተት የሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች ሀላፊነት መሆኑን ማረጋገጥ

ሁሉም የቋሚ ኮሚቴዎች ተግባራቸውን በሚያከናውነበት ወቅት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን ባማከለ መልኩ መሆን ይኖርበታል። በዚሁ መሰረት ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ማለት የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይን በበጀት ሂደት ውስጥ ማካተት በመሆኑ የስርዓተ-ፆታ በጀትን ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ሁሉም ቋሚ ኮሚቴዎች ሃላፊነት ሊሆን ይገባል። ስለሆነም ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን የሁሉም ደረጃ ተቋማዊ ማድረጉ እጅግ ጠቃሚ ነው።

በዚህ ረገድ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ የጋራ ኃላፊነት የሚጠይቅ ሲሆን ሁሉም አካላት በመናበብና በተደራጀ አግባብ ተግባራዊነቱን እንዲያጠናክሩ የሚያስተባብር አካል ያስፈልጋል፡ ፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ሀገራት የተለያዩ መንገዶች ይከተላሉ። ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ የፋይናንስ ጉዳዮች ኮሚቴ ውስጥ ይህንን ጉዳይ የሚከታተል ንኡስ ኮሚቴ ያለ ሲሆን፣ በኡጋንዳ ደግሞ የልዩ ፍላጎት ቡድኖች ኮከስ የሚባለው ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አተገባበርን ይከታተላል። በተጨማሪም የበጀት ቢሮ እና የእኩል እድል ኮሚቴ የተባሉ ሁለት አዳዲስ መዋቅሮችን በመዘርጋት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በዕቅድና በበጀት በአግባቡ ስለ መካተቱ እና የስርአተ ጾታ መካተትን ክትትል ማድረግ ችለዋል።

## 5.4 በተለያዩ ሀገራት ያሉ የፓርላማ አባላት የመካከለኛ ዘመን ማክሮኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ ዝጅግት ላይ ያላቸው ሚና

በብዙ ሀገራት የሚመለከተው የመንግሥት መዋቅር የመካከለኛ ዘመን የበጀት ማዕቀፍ የሚያዘጋጅ ሲሆን፣ በዋናነትም ማዕቀፉ ጠቅላላ ወጪና ገቢ ጣሪያን ግምት እንዲሁም ፋይናንሲንግ ስትራቴጂዎችን የሚያጠቃልል ነው። አንዳንድ ሀገሮች የማክሮ ፊስካል ማዕቀፉን በህግ አውጪው እንዲጸድቅ የሚያደርጉ አሉ። ለምሳሌ በስውዲን ሀገር ፓርላማው ዝርዝር አመታዊ በጀትን ከማጽደቁ በፊት የብዙ አመታት የወጭ ጣሪያ በቅድሚያ ያጸድቃሉ። በአሜሪካም በተመሰሳይ መልኩ ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን፣ ኮንግረሱ የሚያጸድቀው የዓምስት ዓመት ማክሮፊስካል ዒላማ ቢሆንም አስገዳጅ የሚሆነው ግን የመጀመሪያው አንድ ዓመቱ ጣሪያ ብቻ ነው።

## 5.5 የም/ቤቱ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀትን አተገባበርን ክትትልና ቁጥጥር ስራውን እንዴት ማጠናከር ይችላል?

ም/ቤቱ እያንዳንዱ ሴክተር ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በጀት አተገባበር በተመለከተ በየሩብ አመቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ እንዲሁም በሪፖርቱ የቀረቡት አፈጻጸሞችን የመስክ ግምገማ በማከናወን የክትትል ስራውን እንዲያጠናክር ይመከራል።

የፕሮግራም ውጤቶች በሚገመገሙበት ጊዜ ተጠቃሚዎቹ እነማን እንደሆኑ በፆታ በተከፋፈለ መልኩ መረጃ እንዲያቀርቡ በመጠየቅ ለስርአተ ጾታ ምላሽ ሰጪ በሆነ መንገድ ክትትሉን ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ።



# እዝል1፡ አንዳንድ ከበጀትና ከሥርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዙ ጽንሰ ሀሳቦች ምንነት

## 1.1 የኢትዮጵያ የበጀት ሂደት

የኢትዮጵያ መንግስት የፊስካል ፖሊሲ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማፋጠንና ብሎም ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የተለያዩ ጥረቶችን አድርጓል፡፡ በዋናነትም የመንግስት የወጪ በጀት እንደ ዋና መሳሪያ በመጠቀም በተለይም ልማትን በሚያፋጥኑ መሠረተ-ልማቶች ላይ ትኩረት ባደረገ መልኩ ተግባራዊ የተደረገው የፊስካል ፖሊሲው ለኢኮኖሚ ልማት አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል፡፡ ለተከታታይ እየጨመረ የመጣው የመንግሥት ወጪና የወጪ ይዘት ሲታይ በዚህ ረገድ የነበረው ፖሊሲ ከሀገሪቱ ፊስካል ፖሊሲ አንጻር ዘርፈ ብዙ ሚና እንደነበረው የሚያሳይ ነው፡፡

የበጀት ሂደትን ስንመለከት የማክሮኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፉ በሚኒስትሮች ም/ቤት ከጸደቀ በኋላ ለሁሉም የባለበጀት መ/ቤቶች በሚሰጣቸው ጣሪያ መሠረት የበጀት ጥያቄአቸውን ያቀርባሉ፡፡ በመቀጠልም የበጀት ስሚ የሚካሄድ ሲሆን፣ የገንዘብ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች በተገኙበት የባለበጀት መ/ቤቶች ኃላፊዎች ዝርዝር ማብራሪያ በመስጠትና ውይይት በማካሄድ ከሥምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡ በዚህም መሠረት የበጀት ስሚ ከተጠናቀቀ በኋላ የገንዘብ ሚኒስቴር ረቂቅ በጀት በማዘጋጀት በሚኒስትሮች ም/ቤት እንዲደገፍ ያቀርባል፡፡ ከዚያም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውይይት ከተደረገበት በኋላ የተደገፈው በጀት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወያይቶበት እንዲያጸድቀው ይቀርባል፡፡ በም/ቤቱ የጸደቀው ዓመታዊ በጀት በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትሞ ይወጣል፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ 970/2008 (የተሻሻለው) እና 648/2001 መሰረት የእንዳንዱ የመንግሥት መ/ቤት የውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል የመ/ቤቱን የሥራ ክዋኔ ለመገምገም እንዲሁም የመ/ቤቱን ገንዘብና ንብረት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ በተወሰነ የጊዜ ልዩነት ኦዲት ያደርጋል፣ የኦዲት ሪፖርቱን ለመ/ቤቱ በላይ ኃላፊና ለሚኒስትሩ ያቀርባል፣በግኝቱ መሠረት እርምጃ መውሰዱን ይከታተላል፡፡ ስለሆነም የውስጥ ኦዲቱ በገንዘብ አጠቃቀም ላይ ሚና ያለው በመሆኑ ሥራ ላይ የዋለውን ገንዘብ በበጀት ሰነዱ ላይ በተቀመጡ የአፈጻጸም መለኪያዎች ጋር በማነጻጸር መገምገም ይችላል፡፡

## 1.2. የፕሮግራም በጀት

በአትዮጵያ ዘመናዊ የበጀት ሥርዓት ተግባራዊ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ለረጅም ዓመታት በዝርዝር የወጪ አርዕስት ላይ የተመሰረተ የበጀት አሰራር ተግባራዊ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህ የበጀት አሰራር በዋናነት መሰረት የሚያደርገው የቀዳሚ ዓመት የበጀት አፈጻጸም ላይ ነው፡፡ በዚህም ዓመታዊ በጀቱን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግና ሰፊውን የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደርን ለማሻሻል ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ የፕሮግራም በጀት አሰራር ሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ የፕሮግራም በጀት አሰራር በጀትን ከማስተዳደር አንጻር ትልቅ ፋይዳ ያለው ሲሆን፣ በጀትን ይበልጥ ስልታዊ እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡

በተሻሻለው የፕሮግራም በጀት ማኑዋል ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ከፕሮግራም ምስረታ እስከ አመላካቾች ድረስ በእያንዳንዱ ደረጃ እንዲታይ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ለአብነትም የፕሮግራሞች ቅድም ተከተል በሚወጣበት ወቅት የተወሰነ መመዘኛዎች ሥራ ላይ የሚውሉ ሲሆን፣ የሥርዓተ-ፆታ ልማት አንዱ መመዘኛ ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ

ማኑዋሉ ላይ ሥርዓተ-ፆታ ተኮር የሆኑ አመላካቾች እንደሚዘጋጁ ከነምሳሌአቸው የተቀመጠ ሲሆን ፍትሃዊነት ዕይታም ማኑዋሉ ምላሽ ከሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ ነው፡፡

## 1.3 ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት

የመንግሥት በጀት በዋናነት የመንግሥትን ፖሊሲ በውጤታማነት ለማስፈጸም ዋና መሣሪያ ከመሆኑም በላይ መንግሥት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የፊስካል፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዓላማዎች የሚታይበት ነው፡ ፡ ከዚህ የተነሳ በማህበረሰቡ የቀን ተቀን ህይወት ላይ የተለያየ ፋይዳ የሚኖረው ሲሆን፣ በተለይም ሴቶችና ወንዶች በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉአቸው ሚና፣ ኃላፊነት እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጡአቸው ጉዳዮች የተለያየ ከመሆኑ የተነሳ ከተመደበው በጀት እኩል ተጠቃሚ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በጀቱ የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶች፣ ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮች እና የሚያጋጥሙአቸውን ተግዳሮቶችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የሚዘጋጅና ሥራ ላይ የሚውል ከሆነ አሁን ያለው የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ክፍተትን ለማጥበብ እንደ ዓይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡ ይህም ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራርን ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት አሰራር የሴቶችንና የወንዶችን ፍላጎቶችን እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮች ባገናዘበ መልኩ በጀት ለማዘጋጀት የሚያግዝ አካሄድ ነው፡፡ በዋናነትም ትኩረት የሚያደረገው የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ በበጀት ሂደት ውስጥ ማካተትን ሲሆን፣ እነዚህም በዕቅድ ዝግጅት፣ በማጽደቅ ሂደት፣ በአተገባበር ላይ እንዲሁም በክትትልና ግምገማ ባሉት ደረጃዎች ሁሉ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ ባማከለ መልኩ ተፈጻሚ ማድረግን ነው፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ መንግሥት ገቢን የሚሰበስብበት መንገድ በሴቶችና ወንዶች ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖን በመተንተን የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መዛባት እንዳያባብስና ክፍተቱን በሚያጠብ መልኩ ተግባራዊ ማድረግን ያካትታል፡፡

### 1.3.1 የመንግሥት ወጪ ማዕቀፎች

የመንግስት ወጪ ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ለመተንተንና ለመገምገም በሰፊው ጥቅም ላይ የዋሉት ሁለቱ ማዕቀፎች ማለትም የአውስትራሊያና የደቡብ አፍሪካው ማዕቀፎች ሲሆኑ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

#### ሀ. የአውስትራሊያ (ሮንዳ ሻርፕ) ሶስቱ የወጪ ምድቦች ማዕቀፍ

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ከመስጠት አንጻር የአውስትራሊያው የሴቶች በጀት ወጪዎችን በሶስት ይከፍለዋል፡፡

**1.)** ሴቶችን (ሥርዓተ-ፆታን) በተለየ ሁኔታ ዒላማ ያደረገ ወጪ፡- የዚህ ዓይነት ወጪ የሚያተኩረው ተግባራዊ የሚሆኑት ፕሮግራሞች በባህሪያቸው በሴቶች ወይም ወንዶች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆን ነው፡፡ ለምሳሌ ከወሊድ ጋር በተያያዘ የእናቶችን ጤና ሁኔታ ለማሻሻል የሚመደበው ወጪ፣ ሴቶች በብዛት በተሰማሩበት የስራ መስክ ላይ ለሚሰሩ ስራ ፈጣሪዎች ብድር አቅርቦት መስጠት፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሳደግ የሚወጣ ወጪ ወዘተ የሚያጠቃልል ነው፡፡

**2.)** እኩል የሥራ ዕድል በፐብልክ ሰርቪሱ፡- ይህ ዓይነት ወጪ የሚያተኩረው በፐብሊክ ሰርቪሱ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈንና እኩል የሥራ ዕድል መፍጠርን ያለመ ነው፡፡ ለምሳሌ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የወሊድ ፈቃድ፣ ለሰራተኞች ልጆች የሚቀርብ የህጻናት ማቆያ አገልግሎት፣ ልዩ ስልጠና ለሴት ሰራተኞች ወዘተ ጋር በተያያዘ የሚመደበው በጀትን ያጠቃልላል፡፡

**3.)** አጠቃላይ ወይም ሥርዓተ-ጾታን ያካተተ ወጪ፡- የዚህ ዓይነት ወጪ የሚያተኩረው ከላይ ከተጠቀሱት ከሁለቱ ማዕቀፎች ውጭ ያሉትን ሁሉ ሲሆን፣ በዋናነትም ተቋማት ምርትና አገልግሎታቸውን ለህብረተሰቡ በሚቀርቡበት ጊዜ የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ ባማከለ መልኩ ያቀረቡ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማቱን 99 በመቶ በዚህ ምድብ የሚመደበው በመሆኑ በዚህ ምድብ ያሉ ፕሮግራሞችንና ተግባራትን ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ እንዲሆን ማድረጉ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መስፈን የሚኖረው ፋይዳው የላቀ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው ትልቁ ችግር የመንግሥት አካላቱ በጾታ የተከፋፈለ መረጃ በአግባቡ አለመያዛቸው ነው፡፡

ሥርዓተ-ፆታን ያማከለ ወጪ በዋናነት የመንግስት በጀቱ ለሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መስፈን ያለውን ሚና ማየትንና በዚህም የወንዶችና የሴቶች የተለዩ ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ ለትምህርትና ለጤናው ዘርፍ የሚመደበው በጀት መጨመር ሴቶችንና ህጻናትን በበለጠ ሁኔታ ተጠቃሚ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ይህ ግን የሚሆነው ከላይ እንደተጠቀሰው ሴቶችና ወንዶች ያሏቸውን ልዩ ፍላጎቶችንና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ያስገባ እንደሆነ ነው፡፡

### ለ. የደቡብ አፍሪካው ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ሞዴል

የደቡብ አፍሪካው ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት ሞዴል አምስት ተከታታይነት ያሏቸው ደረጃዎች አሉት፡፡ እነዚህም፡-

### 1. ነባራዊ ሁኔታን መተንተን

ይህ የሚያተኩረው ሴቶችና ወንዶች በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉበትን ነባራዊ ሁኔታን በጥልቀት ማየትን ሲሆን፣ በዚህም ምላሽ ማግኘት ያለባቸውን ዋና ዋና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን መለየት የሚያጠቃልል ነው፡፡ ለምሳሌ፡ - ለተለያዩ አገልግሎቶች ያሉአቸውን ተደራሽነት፣ የአገልግሎቶች ጥራት፣ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡ ይህን በሴክተር ደረጃ በምናይበት ጊዜ በሴክተሩ ዒላማ የሚደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ሴቶችንና ወንዶችን) ነባራዊ ሁኔታቸውን በመተንተን በቀጣይ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ግብዓት መውሰድን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ፡- የእናቶች የወሊድ ምጣኔ ሞትን መረጃ፣ የጨቅላ ህጻናት ሞት መረጃ፣ የሴቶችንና የወንዶችን ትምህርት መጠነ ማቋረጥ መረጃ ወዘተ በመሰብሰብና በመተንተን ለቀጣይ እርምጃ መነሻ የሚሆኑ ትንታናዎችን ማካሄድን ያጠቃልላል፡፡

### 2. የፖሊሲ ትንተና

ፖሊሲዎችን ከሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪነት አንጻር የሚከተሉትን ነጥቦች በማንሳት መገምገም፡-

ፖሊሲው በነባራዊ ሁኔታ ለተነሱት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች ምላሽ የሰጠ ነው ወይ?

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ፖሊሲው ያስቀመጠው አቅጣጫ አለው ወይ?

ይህ ከሆነ አመርቂና በቂ በሆነ ሁኔታ ችግሩን ይፈታል?

ፖሊሲው የሚፈለገውን ውጤት እያመጣ ካልሆነ ምን መደረግ አለበት?

### 3. የበጀት ምደባ

ፖሊሲዎቹ በበቂ ሁኔታ ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ የሰጡ ከሆነ ለአፈጻጸማቸው ደግሞ አስፈላጊው ሀብት ሊመደብ ይገባል፡፡ የሚከተሉት ነጥቦች የበጀት ምደባ ሁኔታን ለማየት ይጠቅማሉ፡-

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ ለሆኑ ፖሊሲዎች ሀብት ተመድቧል?

ተመደበው ሀብት በቂ ነው?

### 4. የወጪ አፈጻጸሙንና አገልግሎት አሰጣጡን መከታተል

ከላይ እንደተጠቀሰው በመጀመሪያ ፖሊሲዎቹ በየሴክተሩ ያሉትን የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን ምላሽ መስጠትና ለአፈጻጸማቸው እንዲሁም በቂ ሀብት ሊመደብ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የተመደበው ሀብት በወቅቱ መለቀቅ ያለበት ሲሆን፣ ገንዘቡም ለታለመለት ኣላማ ብቻ መዋል የግድ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንጻር ገንዘቡ በትክክል መለቀቁን፣ በዕቅዱ መሠረት ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የፊዚካል ሥራዎችን አፈጻጸም ጨምሮ አስፈላጊውን ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 5. የረጅም ጊዜ ውጤቶችን መገምገም

ሥራ ላይ የሚውለው ገንዘብ የተፈለገውን ውጤት ሊያስገኝ ይገባል፡፡ ስለዚህ ፖሊሲ እና ሥራ ላይ የዋለው ሀብት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማረጋገጥ መንግሥት የገባዉን ቃል ኪዳን ከመደገፍ አንጻር ያለውን ፋይዳ ትንተና ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ለጤና ሴክተር የተመደበው ሀብት መጨመሩ የእናቶችንና የጨቅላ ሕጻናት ሞት ቀንሷል ወይ? በሌላ አባባል ዒላማ በተደረገው አካል ላይ ፋይዳው የሚፈለገው ደረጃ ተገኝቷል ወይ? የሚለውን መገምገም ተገቢ ነው፡፡

## 1.3.2 የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች

የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ ጥቅም ላይ ከዋሉት መሣሪያዎች ውስጥ፡-

ሀ. ሥርዓተ-ፆታ ተኮር ፖሊሲ ምልከታ/ግምገማ፡- ሥርዓተ-ፆታ ተኮር የሆነ ፖሊሲ ግምገማ ማለት የተለያዩ መ/ቤችን ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር መተንተን ሲሆን፣ በዋናነትም እነዚህ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች እንዲሁም ለአፈጻጸማቸው የተመደበው ሀብት በሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ መገምገምን ያጠቃልላል። ይህም የሚነሳው ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር በሴክተሩ ያለውን ነባራዊ ሁኔታን በመተንተን ሲሆን፣ የሥርዓተ-ፆታ ትንተና፣ የሥርዓተ-ፆታ ኦዲት፣ በአጠቃለላይ በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያ የዳሰሳ ጥናቶችን በማካሄድ ነው። የሚከተሉት ማገናዘቢያዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡-

ፖሊሲዎቹና ፕሮግራሞቹ ሥርዓተ-ፆታ ተኮር ነባራዊ ሁኔታ ትንተና ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው? የሴቶችንና የወንዶችን የተለያየ ፍላጎት እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ አስገብቷል?

ሴቶችና ወንዶች ከሚሰሩት ሥራ አንጻር የሰዓት አጠቃቀማቸው ሁኔታ ከግምት ውስጥ ገብቷል?

ፖሊሲዎቹና ፕሮግራሞቹ ሴቶች/ወጣቶች በስራ ፈጠራ ያላቸውን ተሳትፎ የተሻለ እንዲሆን አስተዋጽኦ ያደርጋል?

በአጠቃላይ የተመደበው ሀብት ድህነትን ለመቀነስና ሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ለማስፈን ያለውን ቁርጠኝነት የሚያንጸባርቅ ነው?

በአጠቃላይ የተመደበው ሀብት የሴቶችንና የወንዶችን የተለያየ ፍላጎት እንዲሁም ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ አስገብቷል?

ለፕሮግራሞችና ለፕሮጀክቶች የተመደበው ሀብት የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መዛባትን ይቀንሳል ወይስ ያሰፋል?

ለ. ሥርዓተ-ፆታ ተኮር የተገልጋዮች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፡- በዚህ መንገድ ተገልጋዮች በመንግሥት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ዳሰሳ ጥናት የሚካሄድበት ሲሆን፣ በዋናነትም የተለያየ ፍላጎቶችና ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮች በምን ደረጃ እንደታየ ከራሳቸው አንደበት የሚንሰማበት መንገድ ነው። የዚህ ትንተና ዋና ዓላማው መንግሥት ከሚሰጣቸው አገልግሎት ማን እና ምን ያህል ተጠቃሚ እንደሆኑ መረጃ ለማግኘት ነው። ለምሳሌ ከጤና አገልግሎት አቅርቦት ሴቶችን ምን ያህል ተጠቃሚ እንደነበሩ ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በቀጣይ ለሚወስደው እርምጃ እንደ ግብዓት ሊወስድ ይችላል፡ ፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ዋና ጉዳይ የዳሰሳ ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ መረጃዎች የሚሰበሰብበት መንገድ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይን ያማከለ ሊሆን ይገባል።

ሐ. በፆታ የተከፋፈለ የተጠቃሚዎች ትንተና፡- የዚህ ትንተና ዋና ዓላማው መንግስት ለዜጎች የሚሰጣውን አገልግሎቶች መነሻ በማድረግ ከአገልግሎቶቹ ሴቶችና ወንዶች ምን ያህል ተጠቃሚ እንደነበሩ ለመገመት ነው፡፡ በዚህም መሰረት የተጠቃሚነት ደረጃቸውን ትንተና በማድረግ መንግስት ከሚያቀርባቸው አገልግሎቶች ይበልጥ ተጠቃሚ የሆኑት ሴቶች ወይስ ወንዶች? በአግባቡ ተጠቃሚ ያልሆኑትስ ለምን የሚለውን ለመመለስ ያግዛል፡፡

መ.በጾታ በተከፋፈለ ትንተና በጊዜ አጠቃቀምና በበጀት ፋይዳ፡- የዚህ ትንተና ዋና ዓላማ በመንግስት በጀትና በቤት ውስጥ በሚሰራው ስራ መካከል ያለውን ግንኙነት መተንተን ሲሆን፣ በተለይም ክፍያ የማይከፈልበት የቤት ውስጥ ስራ ሁኔታ በፖሊሲ ትንተና ወቅት ከግምት ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ ነው፡፡ ትንተናውም የሚያተኩረው መንግሥት የሚመድበው በጀት በወንዶችና በሴቶች የጊዜ አጠቃቀማቸው ላይ የሚኖረውን ፋይዳ ሲሆን፣ ለምሳሌ መንግስት ለህዝቡ የሚሰራቸው የተለየዩ መሰረተ-ልማቶች የሴቶችን የሥራ ጫና በመቀነስ ጊዜአቸውን እንዲቆጥቡና ምርታማ በሆኑ ተግባራት እንዲያውሉት ያግዛቸዋል፡፡ በተጨማሪም ለምሳሌ በጤና ተቋማት የሚሰጠው የጤና አገልግሎት በዝቅተኛ ዋጋ ሲሆን ወይም የህጻናት እንክብካቤ ማዕከላት ዋጋ ዝቅተኛ ቢሆን ሴቶች ተጨማሪ ጊዜ ስለሚያገኙ ሌሎች ምርታማ በሆኑ ተግባራት ስለሚሰማሩ የሀገሪቱ አገራዊ ምርቱ (GDP) እንዲጨምር ያደርጋል፤ በዚህም ሴቶች ለአገራዊ ምርት የሚያበረክቱትን ድርሻ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

ረ.ሥርዓተ-ፆታ ተኮር መካከለኛ ዘመን የማክሮ-ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፍ፡- ይህ አካሄድ በመካከለኛ ዘመን ፊስካል ማዕቀፍ እና በኢኮኖሚ ሞዴሎች ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲካተት ማድረግን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ይህንን ለማድረግ ከሚጠይቃቸው እርምጃዎች ውስጥ የመንግሥትንና የህዝቦችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሥርዓተ-ፆታ ላይ የሚኖረውን ፋይዳ መለካት፣ የኢኮኖሚን አንቅስቃሴን ከሥርዓተ-ፆታ አኳያ ለማየት አዳዲስ መለኪያዎችም ማካተት፣ ክፍያ የማይከፈልባቸውን የቤት ውስጥ ሥራዎችን በሞዴሎች ውስጥ ማካተት፣ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ታሳቢዎችን ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር ማየት ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም በዋናነት ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በተቻለ መጠን መረጃዎችን በፆታ የተከፋፈለ እንዲሆን በማድረግ ሲሆን፣ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ያላቸውን የወንዶችንና የሴቶችን የተለያዩ ሚናዎች ለይቶ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ የመካካለኛው ዘመን የማክሮ-ኢኮኖሚና ፊስካል ማዕቀፉ በጾታ በተከፋፈሉ መረጃዎች መሰረት ባደረገ መልኩ እየተሰራበት መሆኑን ለመገምገም ጥቅም ላይ የዋለ የሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀት መሳሪያ ነው፡፡

ሰ. በፆታ የተለየ የታክስ ሁኔታ ትንተና፡- የዚህ ትንተና መሣሪያ ዋና ዓላማው ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ በተለያዩ የህብረተሰቡ ክፍሎች ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ መተንተን ሲሆን በዚህም እኩልነት እንዳይሰፍን የሚያደርገውን ማንኛውንም አሉታዊ የታክስ ፖሊሲ ተፅዕኖን ለመቀነስ ነው፡ ፡ መንግሥት ገቢን የሚሰበስብበት መንገድ (ቀጥታ ታክስ እንደ ገቢ ግብር ያሉ እንዲሁም ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች እንደ ተጨማሪ እሴት ታክስ ያሉ) በሴቶችና በወንዶች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ትንተና ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ሴቶች ማህበረሰቡ ከሰጣቸው ሚና የተነሳ የቤት ውስጥ አስቤዛ የመግዛት ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ የተጨማሪ እሴት ታክስን በፍጆታ ዕቃዎች ላይ በሚጣልበት ጊዜ ተጽዕኖው በአግባቡ ከግምት ውስጥ ካልገባ ጫናው ይበልጥ ሴቶች ላይ ሊሆን ይችላል፡፡

ሸ. ሥርዓተ-ፆታ ተኮር የበጀት መግለጫ ሪፖርት፡- የመንግስት አካላት ፖሊሲዎቹ፣ ፕሮግራሞቹና ሥራ ላይ የዋለው ሀብት ከሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ግብ አንጻር ባመጣው ለውጥ ዙሪያ የተጠያቂነት ሪፖርት የሚያቀርቡበት ነው፡፡ በዚህም በተለይ ለዓመቱ በተመደበው በጀት ምክንያት ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር የመጣው ለውጥ ዙሪያ ተገቢውን መረጃ መስጠቱ ተገቢ ነው፡፡ ይህም ጠቅላላ በጀቱን ወይም የተወሰኑ ሴክተሮችን እንደ ምሳሌ በመውሰድ የተመደበው በጀትና የተሰበሰበው ገቢ በወንዶችና በሴቶቹ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ተንትኖ ማቅረብ ይቻላል፡፡ ይህ ማለት አጠቃላይ የመንግስት በጀቱ (የገቢና የወጪ በጀት) እንዲሁም ለሴክቴሮች የሚመደበው በጀት ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር የሚያመጣውን ለውጥ በግልጽ ማስቀመጥ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የጤና አገልግት ዋጋ መጨመር ከወንዶቹ ይልቅ ደሀ በሆኑ ሴቶች ላይ ተጽዕኖው ይበረታል፤



# እዝል 2፡- ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ምላሽ ሰጪ በጀትን ተግባራዊ ለማድረግ መሠረት የሚሆኑ ብሔራዊና ዓለምዓቀፍ መሳሪያዎች

## 2.1 ዓለምዓቀፋዊ ሥምምነቶች

ኢትዮጵያ የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ለማስፈንና ሴቶችን ለማብቃት የሚያስችሉ ዓለምዓቀፋዊና አህጉራዊ ሥምምነቶችን አድርጋለች፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የሴቶችን የፖለቲካዊ መብትን ለማረጋገጥ የተፈረመ ሥምምት/CPRW/፡- ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ1969 በፈረመችው ሥምምነት ማንኛውም ሰው በሀገሩ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በውክልና የመሳተፍ፣ የህዝብ አገልግሎቶች እኩል ተደራሽ መሆን፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተርና በሰብዓዊ መብት ድንጋጌ መሠረት ሴቶችና ወንዶች በእኩልነት የመኖር እና በፖለቲካ እንቅስቃሴ እኩል የመሳተፍ መብትን የሚያጎናጽፍ ነው፡፡

በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም መድሎዎችን ለማስወገድ የተፈረመ ስምምነት /CEDAW/፡- እ.ኤ.አ በ1981 ኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ማናቸውንም መድሎዎችን ለማስወገድ አለም አቀፍ ስምምነቶችን ከፈረሙ ሀገሮች አንዷ ናት፡፡ በዚህም ጾታዊ መድሎ መኖሩን ወይም እኩልነት አለመኖሩን በመገንዘብ መንግሥት ጣልቃ በመግባት አስፈላጊውን ሁሉ እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኝነቱን ያሳየበት ነው፡፡

የቤጂንግ የድርጊት መርሃ-ግብር፡- በዚህ የድርጊት መርሃ-ግብር መሠረት ልማትን፣ ሠላምንና ማህበራዊ ፍትህን ለማረጋገጥ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት መስፈን የማይተካ ሚና ያለው መሆኑን ነው፡፡ የድርጊት መርሃ-ግብሩም የሰዎችን ሁሉ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዱ 12 የትኩረት አቅጣጫዎችን ለይቶ ያስቀመጠ ሲሆን፣ እነዚህም ሴቶችና ድህነት፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ጥቃት፣ ግጭት፣ ኢኮኖሚ፣ ውሳኔ ሰጪነት፣ የሴቶችን ህይወት ማሻሻል፣ የሴቶች ሰብዓዊ መብት፣ የብዙዓን መገናኛ፣ አካባቢና ህጻናት ሴቶች ከሚባሉ ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያሏቸው ናቸው፡፡

ለሥርዓተ-ፆታ ምላሽ ሰጪ በጀትን በተመለከተ የድርጊት መርሃ-ግብሩ በአንቀጽ 345 ላይ እንደሚከተለው አስቀምጦታል፡፡

'' .... የድርጊት መርሃ-ግብሩን ለማሳካት በሀገራና በዓለም አቀፍ ደረጃ በቂ ሀብትን ማሰባሰብ በተለይም ለታዳጊ ሀገሮች የሚውል ተጨማሪ በጀትን ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከሀገራዊ ተቋማትና ከበጎ አድራጊ ግለሰቦች ማግኘት ያስፈልጋል፡፡ የተገኘውም ገንዘብ የሴቶችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ለሚሰሩ አገራዊ፣ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ተቋማትን አቅም ለመገንባት፣ ለሴቶችንና ወንዶችን በሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ አካላትና ፖሊሲ የማውጣት ሂደት ውስጥ እኩል መብት፣ ተሳትፎ፣ ኃላፊነትና ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ተጠያቂነት ያለውን ሥርዓት ለመዘርጋትና ለማጠናከር ይውላል፡፡ በተጨማሪም ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለማስፈጸም የሚመደበው በጀት የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ያማከለ ሊሆን ይገባል፡፡

በአንቀጽ 346 ላይ ደግሞ፡- ''የድርጊት መርሃግብሩን ስትራቴጂያዊ ዓላማዎችን የማስፈጸም ዋናው ኃላፊነት የመንግሥት ነው፡፡ እነዚህንም ዓላማዎች ለማሳካት መንግስት ከሚመድበው በጀት ሴቶች በተገቢ ሁኔታ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ መቀየስ የሚገባው ሲሆን፣ በዚህም የሴቶችን ምርታማነት ለማጎልበትና

ማህበራዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማርካት ከሥርዓተ-ፆታ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ የተፈረሙትን ሥምምነቶችንና ሌሎች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውሳኔዎችን ለመተግበር ቁርጠኝነትን ማሳየት ይገባል።"

እንዲሁም በአንቀጽ 347 "የድርጊት መርሃ-ግብሩን አፈጻጸም ለሚከታተሉ በአገር ውስጥ በሴቶች ዙሪያ ለሚሰሩ መዋቅሮች በቂ ሀብት መመደብን ያስፈልጋል።"

የ2030 ዘላቂ ግቦች አጀንዳ፡- ይህ ዓለም አቀፋዊ ማዕቀፍ በዋናነት በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በአከባቢያዊ አቅጣጫዎች ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ሲሆን፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ማስፈንና ሴቶችን ማብቃት በሚመለከት ራሱን የቻለ ግብ አለው። በተጨማሪም የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ዒላማዎች በሌሎቹ መለኪያዎች ውስጥ የተካተተ ሲሆን በፆታ የተከፋፈለ መረጃ መኖር እንደሚገባ ያስቀምጣል። አጀንዳውም የሚያተኩርባቸው ጉዳዮች፡- ድህነት አልባነት፣ ጠኔ አልባነት፣ ጥሩ የጤና ሁኔታ፣ጥራት ያለው ትምህርት፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት፣ ንጹህ ውሃ፣ ንጹህና ተደራሽ የሀይል ምንጭ፣ ምቹ ሥራና ኢኮኖሚ ዕድገት፣ መሰረተ-ልማትና የኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ የኢ-ፍትሀዊነትን መቀነስ፣ ዘላቂ ከተሞችና ማህበረሰብ፣ መጪውን ትውልድ ከግምት ያስገባ የሀብት አጠቃቀም፣ የአየር ንብረት ለውጥን መከላከል፣ ከውሃ በታች ያሉ ህይወት ያላቸው አካላት ህይወት፣ በምድር የሚኖሩ ህይወት ያላቸው እንሰሳት፣ ሠላም፣ ፍትህና ጠንካራ ተቋማት እና አጋርነት ለግቦቹ የሚሉ ናቸው።

### በ2063 አጀንዳ ውስጥ የስርአተ ጾታ አጀንዳ

ይህ አጀንዳ በ2063 በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የሚደርሱ ሁሉም አይነት ጥቃቶች እና መድልኦዎች ተወግደው ሁሉንም የሰብአዊ መብቶቻቸውን እንደሚጠቀሙ፤ በሁሉም መስኮች እኩል እድል ያገኙና ሁሉም መስኮች ተደራሽ የሆነላቸው ሙሉ በሙሉ የበቁ ሴቶችን በአፍሪካ እንደምናይ፤ እንደ መሬት፣ ብድር፣ ግብአት እና የገንዘብ ነክ አገልግሎቶች ያሉ ሀብቶች ከ90 በመቶ በላይ ለሆኑ የገጠር ሴቶች ተደራሽ እንደሚሆን እንዲሁም የስርአተ ጾታ እኩልነት ሙሉ በሙሉ እንደሚከበር ለምሳሌ የሴቶች የመንግስት የስራ አመራትነት ተሳትፎ 50 በመቶ እንደሚሆን አስቀምጧል።

### የአፍሪካ ሰብአዊና ህዝቦች መብት ቻርተር

የአፍሪካ ሰብአዊና ህዝቦች መብት ቻርተር ዓላማ ያደረገው በአህጉር ደረጃ ሰብዓዊ መብትንና ነጻነትን ለማረጋገጥ ነው። በቻርተሩ አንቀጽ 2 ላይ በዘር፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሀይማኖት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም በሌሎች በየትኛውም ምክንያት መድሎ ማድረግ እንደማይቻል ይደነግጋል። በተመሳሳይ በአንቀጽ 18 ሁሉም አካላት በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን መድሎ ለማስቀረት እንዲረባረቡ ጥሪ የሚያደርግ ሲሆን፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሴቶችን መብት በተመለከተ የተደነገጉ ሥምምነቶችን ለማክበር መስራት እንደሚገባ ያስቀምጣል።

## 2.2 አገራዊ የህግና ፖሊሲ ማዕቀፎች

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ምቹ የህግ፣ የአስተዳደርና የፖሊሲ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ዘላቂ ለውጥንና ፍትሀዊ ልማትን ለሚገድቡ የሥርዓተ-ጾታ እኩልነት መዛባት /gender

inequality/ ምላሽ ለመስጠት ቁርጠኛ አቋም ያለው መሆኑን በማያሻማ መልኩ አሳይቷል፡፡ ተግባራዊ ካደረጋቸው አገራዊ የህግና ፖሊሲ ማዕቀፎች መካከል የሚከተሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

## ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ

በ1986 ዓ.ም የተቀረጸው ብሔራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ ዋነኛ አላማዎች በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች ላለው የሥርዓተ-ጾታ እኩል አለመሆን /gender inequality/ ምላሽ መስጠትና ከሥርዓተ-ጾታ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች የሚዳስሱ ቁልፍ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ነው፡፡ በተጨማሪም የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተሉ መዋቅሮች በየደረጃው በሚገኙ ሴክተር መ/ቤቶች እንዲቋቋሙ መሠረት የጣለ ነው፡፡

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ህገ-መንግሥት

የኢትዮጵያ ህገ-መንግሥትመንግስት የሴቶችን መብት በተመለከተ ሰፊ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት በአንቀጽ 6 ላይ እኩል የዜግነት መብት ለሴቶች እና ለወንዶች ያጎናጸፈ ሲሆን በአንቀጽ 7 ደግሞ በሕገ መንግስቱ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው ሁሉ የሴትንም ፆታ እንደሚያካትት ይደነግጋል፡፡ በሕገ መንግስቱ በአንቀጽ 25፣ 34፣ 35 እና 89/7 የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሁሉም መስኮች ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን በማረጋገጥ የሴቶችን መሰረታዊ መብቶች የሚያስጠብቁ ናቸው፡፡ የህገመንግስቱ አንቀጽ 35 በኢኮኖሚያዊ በማህበራዊ፣ በፖለቲካዊና በባህላዊ ዘርፎች ለሴቶች ከወንዶች እኩል መብቶችን ያቀዳጃቸው ሲሆን የደረሰባቸውን የታሪክ አሻራ ለማካካስ የልዩ ድጋፍ እርምጃ እንዲያገኙ ደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ኢትዮጵያ ያጸደቃቻቸው ዓለም አቀፍ ሥምምነቶች ሀገሪቱ የህግ አካል እንደሆኑ የሚደነግግ ሲሆን፣ በዚህም መሰረት ሀገሪቱ ያጸደቀቻቸው አለም አቀፋዊና ክልላዊ ስምምነቶች፤ የፈረመቻቸው ፕሮቶኮሎችና ስምምነቶች፣ የገባቻቸው ግዴታዎች የህገመንግስቷ ወሳኝ አካልና ድንጋጌ የተቀመጠባቸው ናቸው፡፡

## ሥርዓተ-ፆታን ያማከሉ አገራዊ ፖሊሲዎች

ለኢትዮጵያውያን ልጃገረዶችና ሴቶች አመቺ የሆኑና ለሥርዓተ-ጾታ እኩልነት ሚና ተገቢውን ትኩረት የሰጡ በርካታ ፖሊሲዎች የተቀረጹ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የማሕበራዊ ደህንነትና ልማት ፖሊሲ /1988 ዓ.ም/፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ /1986 ዓ.ም/፣ የጤና ፖሊሲ /1985 ዓ.ም/፣ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ /1993 ዓ.ም/፣ የባህል ፖሊሲ /1989 ዓ.ም/፣ የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ፖሊሲ /1989 ዓ.ም/፣ እና ሌሎችም ይገኙባቸዋል፡፡

## የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጆች

የፌዴራል የመንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 መሰረት ሴቶች በቅጥር፣ በደረጃ እድገት፣ በዝውውር፣ በድልድል፣ በትምህርትና በስልጠና ልዩ ድጋፍ የማግኘት እንዲሁም ከሃይልና ከወሲባዊ ጥቃት ነጻ በሆነ የስራ አካባቢ የመስራት ሕገመንግስታዊ መብቶችን ያረጋግጥላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች የደረሰባቸውን የታሪክ አሻራ ለማካካስ የልዩ ድጋፍ እርምጃ እንዲያገኙ ይደነግጋል፡፡

የወሊድ ፍቃድንም ቀድሞ ከነበረበት 90 ቀናት ወደ 120 ቀናት አሳድጓል፡፡ በተጨማሪም ጽንሱ የተቋረጠባቸው ነፍሰጡር ሴቶች የህክምና ማስረጃ በማቅረብ ድህረ ወሊድ ፍቃድ ይሰጣቸዋል፡፡ ወንዶችም የትዳር ጓደኞቻቸው ሲወልዱ ደሞዝ የሚከፈልበት 10 ቀናት ፍቃድ ይሰጣቸዋል፡፡

ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ሴት የመንግስት ሰራተኞች ህጻናት ልጆቻቸውን የሚያጠቡበትና ህጻናቱን የሚንከባከቡበት የህጻናት ማቆያ ማቋቋም እንደአለበት ተደንግጓል፡፡

## የወንጀል ሕግ

የ1949 የወንጀል ሕግ በ1997 የተሻሻለ ሲሆን፣ የቤት ውስጥ ጥቃትን በጋራ የሚኖሩ አጋሮችን ነገር ግን ህጋዊ በሆነ መልኩ ያልተጋቡትን ጨምሮ እንደ ወንጀል እንዲቆጠር የደነገገ ህግ ነው፡፡ የወንጀል ሕጉ የሴቶችን ደህንነት ለማስጠበቅና በሴቶች ላይ ጎጂ ተግባራትን በሚፈጽሙ ሰዎች ላይ ቅጣት ለመጣል በሚያስችል መልኩ ተሻሽሏል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የሴቶች ግርዛት፣ ጠለፋ፣ ያለ እድሜ ጋብቻ፣ አስገድዶ መድፈር ወዘተ ያሉ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በወንጀል ሕጉ ቅጣትን የሚያስከትሉ ተደርገው ተደንግገዋል፡፡

## የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ

በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ በፌዴራል ደረጃ በ1992 ዓ.ም የተሻሻለ ሲሆን የፌደራል ህጉ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች በቀጥታ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ሌሎች ክልሎች ግን በህግ አግባብ የራሳቸውን የቤተሰብ ህግ እንዲያዘጋጁ አልያም ከፌዴራሉ ሕግ ጋር በማጣጣም የራሳቸውን የቤተሰብ ህግ እንዲያወጡ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡ የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ ስለ ሴቶች በርካታ ወሳኝ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ፡-

ህጉ የሴት ልጅን የጋብቻ እድሜ ከ15 ዓመት ወደ 18 ዓመት ከፍ በማድረግ ከወንዶች እኩል እንዲሆን ያደረገ፣

የቤተሰብ ሕጉ ሴቶች መሬትን ጨምሮ የንብረት ባለቤቶች እንዲሆኑ፣ እንዲጠቀሙና እንዲቆጣጠሩ መብት የሰጠ፣

ከዚህ በፊት በነበረው ህግ የማይፈቀደውና የሴቶች ላይ እንደሚፈጸም መድሎ የሚቆጠረው የፍቺ ጉዳይ ሲሆን፣ በዚህ በተሻሻለዉ ህግ መሠረት የትዳር አጋሮቹ አብረው ለመኖር የማይችል ሁኔታ ስኖር በጋራ በመስማማት መፋታት እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡

ፍቺን በተመለከተ በቤተሰብ የሚደረገውን ዳኝነት የሚከለክል ሲሆን፣ ይህም በብዛት የሴቶች መብት እንዲረገጥ የሚያደርግ ነበር፡፡

በተጨማሪም ጋብቻም በተጋቢዎች ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ መፈጸም እንዳለበት ተደንግጓል፡፡



# እዝል 3፡ የተመረጡ ሴክተሮች ዋና ዋና የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችና መፍትሄዎቻቸው

## 3.1 የግብርና ሴክተር

### የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

- የመሬት ባለቤትነት መብት በብዛት በወንዶች እጅ መሆን፤
- እማዎራዎች ያሏቸው የመሬት መጠን ከአባዎራዎች ጋር ሲነጻጸር አነስተኛ መሆን፤
- ያገቡ/ከባሎቻቸው ጋር የሚኖሩ ሴቶች በመሬት ዙሪያ ውሳኔ የመስጠት አቅም/መብት ዝቅተኛ መሆን፤
- ያገቡ/ከባሎቻቸው ጋር የሚኖሩ ሴቶች ለግብርና ኤክስቴንሽን እና ተያያዥ አገልግሎቶች ያሏቸው ተደራሽነት ዝቅተኛ መሆን፤
- በህግ የተደነገገ መብት ቢኖራቸውም በባህላዊ አስተሳሰብ የተነሳ ሴቶች መሬትን በፍቺ ወይም በውርስ ሊተላለፍላቸው አለመቻል፤
- በግብርና ሴክተር በሚገኙ የባለሙያ እና ዲኤ የስራ መስኮች ላይ የሴቶች ተሳታፊነት ከወንዶች ያነሰ መሆን፤
- ሴት አርሶ አደሮች ለተለያዩ መረጃዎች፣ ለግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትና ለብድር ያላቸው ተደራሽነትና ተሳታፊነት አናሳ መሆን፤
- የግብርና ልማት ሰራተኞች የሴት አርሶ አደሮችን ፍላጎትና ችግሮቻቸውን በአግባቡ ያለመረዳት፤
- የሴት አርሰ አደሮች ከግብርና ልማት ባለሙዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ከወንድ አርሶ አደሮች አንጻር ሲታይ ውስን መሆን፤
- ስለ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ ትምህርቶች አባዎራቹ ከሰለጠኑ በኋላ ለእማዎራዎቹ በአግባቡ ይደርሳቸዋል ብሎ ታሳቢ ማድረግ፤ በዚህም ከሚቀርበው የኤክስቴንሽነ አገልግሎቶች ሴት አርሶ አደሮች በአግባቡ ተጠቃሚ አለመሆን፤
- ለአርሶ አደሮች የሚቀርበው መልዕክት የሴቶችን ነባራዊ ሁኔታ (የሥራ ጫናቸውን፣ የቤት ውስጥ ኃላፊነታቸውን፣ ሌሎች ተግዳሮቶቻቸውን) ያገናዘበ አለመሆን፤
- ሴት አርሶ አደሮች ስለ ግብርና ግብዓቶችና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች መረጃ አለማግኘት፤
- ሴት አርሶ አደሮች በግብርና ግብዓቶችና በግብርና ግብዓቶች አጠቀቃቀም ዙሪያ በቂ እውቀት አለመኖር፤
- የግብርና ግብዓቶችን ለመሸመት የሚያስችሉ ገንዘብ ወይም የብድር አገልግሎቶችን ሴት አርሶ አደሮች አለማግኘት፤

- የግብርና ግብዓቶችን ለማግኘት ሴት አርሶ አደሮች ዘንድ የጊዜና የትራንስፖርት ችግር መኖር፤
- ከግብርና ግብዓት ጋር በተያያዘ የሚሰጡ ግብዓቶች ሴት አርሶ አደሮች ከማያመርቷቸዉ ሰብል አይነቶች ጋር በሚሆኑበት ጊዜ ግብዓቶች ያለማግኘት ችግር፤
- ከግብርና ምርት ግብይት ጋር በተያያዘ ወንዶች በዋናነት ምርታቸውን በህጋዊ ገበያ ላይ የሚሸጡ ሲሆን ሴቶቹ ደግሞ በብዛት በሰፈር በሚገኙ ገበያዎች በዝቅተኛ ዋጋ ከመሸ ጣቸው በተጨማሪ ለገበያው የሚያቀርቡት የምርት መጠኑም አነስተኛ መሆን፤

## የመፍትሄ እርምጃዎች

- እማወራዎች እና ባለትዳር ሴቶች በግል እና በጋራ ለያዙት መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንዲያገኙ ማድረግ፤
- የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት የሚያገኙበትን አሰራር ቀላልና ለሴቶቹ ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፤
- የይዞታ ማረጋገጫ ባለቤት የሆኑ ሴቶች መሬቱ ራሳቸውን በሚጠቅም መልኩ እየተጠቀሙበት መሆኑን ማረጋገጥ
- በየደረጃው በሚዋቀረው የመሬት ይዞታ ኮሚቴ ሴቶች እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- መሬት የሌላቸው ሴቶች መሬት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
- በግብርና ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ እንዲካተት ማድረግ፤
- ሴቶች በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች ያላቸውን ተሳትፎ ማጎልበት፤
- የኤክስቴንሽን ስልጠናዎች ሲደረጉና የሰልጣኞች ምልመላ ሲደረግ ዝቅተኛ የእማዎራዎች የተሳትፎ መጠን ማስቀመጥ፤
- ሴቶች በኤክስቴንሽን ስልጠናዎች ላይ እንዲሳተፉ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፤
- የግብርና ልማት ባለሙያዎች ለእማዎራዎቹ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን በሚያቀርቡበት መንገድ ሥልጠና መስጠት፤
- በአዲስ በሚቀረጹ የኤክስቴንሽን ፕሮግራሞች ላይ ሴቶች እንዲሳተፉ ማበረታታት፤
- ለሴቶች ምቹ የሆኑ የገንዘብ/ብድር አቅርቦቶችን ማመቻቸት፤
- ለሴቶች ምቹ የሆነ /ጊዜንና ጉልበትን የሚቆጥቡ/ ቴክኖሎጂዎችን ለሴት አርሶአደሮችና አርብቶአደሮች ማዘጋጀት፣
- ሴቶች በግብርና ለሚያመርቷቸው ምርቶች በቂ ገበያ ማመቻቸት፤ በአገር አቀፍም ሆነ በክልሎች ደረጃ ከሚዘረጋው የገበያ ኔትወርክ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤

- ሴቶች በእርሻ ልማትና በአግሮ ፕሮሰሲንግ ስራዎች በብቃት እንዲሳተፉና ምርትና ምርታማነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና የተለያዩ የውሀ አማራጮችን በመጠቀም ምርታማነታቸውን ማሳደግ፤
- እንደ የሴቶች የልማት ቡድን፣ የግብርና የህብረት ስራ ማህበራት፣ የራስ አገዝ ማህበራት፣ የቁጠባና የብድር ማህበራት እንዲሁም የሴቶች የህብረት ስራ ማህበራት ባሉ ቡድኖች እንዲሳተፉ ማበረታታት፤

## 3.4 የስራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና

### የስርአተ ጾታ ጉዳዮች

- የሴቶችና የወንዶችን ፍላጎቶችን፣ ተግዳሮቶችንና ቅድሚያ የሚሰጡአቸውን ጉዳዮች ለይቶ አለማወቅ፤
- የስራ አጥነትና ለሴቶች ተስማሚ አገልግሎቶች አለመስፋፋት፤
- ስራ አጥ ለሆኑ ሴቶች የሚሰጡ ስልጠናዎች ተመሳሳይ መሆን፣ የሴቶች ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ስራዎች ላይ ማተኮርና የሀገሪቱን የገበያ ሁኔታ ያገናዘበ አለመሆን
- በኢ-መደበኛ የንግድ መስኮች ላይ የተሰማሩ ሴቶችን ወደ መደበኛው የንግድ ስርአት እንዲገቡ ለማድረግ የሚያስችል የድጋፍ ስርአት አለመኖር፤
- ሴቶች ኢንተርፕራይዞችን ከአነስተና ወደ መካከለኛ ብሎች ወደ ከፍተኛ ሽግግር እንዲያደርጉ የሚሰጠው ድጋፍ የተጠናከረ አለመሆን፤
- የማምረቻ፣ የመሸጫ ቦታና የመሰረተ ልማት አውታሮች አለመስፋፋት፤
- የገበያ ትስስር፣ የድጋፍና ክትትል ቀጣይነት ባለው መልኩ አለመቅረብ፤
- በኢኮኖሚ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ቀረጻ፣ ትግበራ ክትትልና ግምገማ ሂደት ሴቶችን ተሳታፊ በማድረግ ረገድ ውስንነት መኖር፣
- የከተማ የስራ አጥነት ምጣኔ የሴቶቹ ከወንዶቹ መብለጡ፤

### የመፍትሄ እርምጃዎች

- በከተማ የስራ እድል በመፍጠር የሴቶችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
- ሴቶች ተደራጅተው ወይም በግል በአነስተኛና መካከለኛ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እንዲሰማሩና ሽግግር እንዲያደርጉ መርዳት፤
- መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንዲሁም በግለ ክ/ኢኮኖሚና በህጋዊ መንገድ በውጭ ሀገር በተለያዩ መስኮች በመቀጠር መስራት ለሚፈልጉ ሴቶች ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት የስራ እድል እንዲያገኙ ማድረግ፤

- በኢ-መደበኛ ንግድ ለተሰማሩ ሴቶች አስፈላጊና ወቅታዊ ድጋፎችን በማድረግ ወደ መደበኛ ንግድ ማሸጋገር
- የወጣቶች የስራ ፈጠራ ለማጎልበት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የወጣት ሴቶችን እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤
- ከድህነት ወለል በታች ያሉ ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግና የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ለሴቶች የስራ እድል የሚፈጥሩ ፕሮራሞችን መተግበር፤
- መስራት እየቻሉ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች በልማታዊ ሴፍቲኔትና በሌሎች ፕሮግራሞች እንዲታቀፉ ማድረግ፤
- የመስራት አቅም የሌላቸውና በምግብ ራሳቸውን ያልቻሉ ሴቶች የቀጥታ ሴፍቲኔት ድጋፍ በመስጠት መሰረታዊ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤ሴቶች በቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣
- ለሥራ ፈላጊዎች የሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘዴዎች የሴቶችን ፍላጐት ማገናዘብ፣
- ለሥራ ፈላጊዎች የሚለዩ የሥራ እድል አማራጮች የሴቶችን ፍላጎትና ሁኔታ ማገናዘብ
- ለሥራ ዕድል ፈጠራ የሚሰጡ የቴክኒክና ክህሎት ስልጠና፤ መረጃና ምክር ለሴቶች ተደራሽነትና ምቹ መሆን፣
- በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች /የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ/ ለሴቶች ተደራሽ እና ፍላጎት መላሽ መሆን፣
- በሴቶች የሚመሩ የኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ ሽግግር በሚፈለገው ደረጃ ማድረስ
- በማህረሰብ ልማት ሥራዎች ህፃናት ላላቸው እናቶች ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የሚቀረፁ ፕሮጀክቶች ችግር ፈቺ እና ፍላጎታቸውን ምላሽ መስጠት፣ እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ማንዋሎች እና ሪፖርቶች የሴቶችን ተጠቃሚነት ማሳየት፣
- በሥራ እድል ፈጠራና በምግብ ዋስትና ተጠቃሚዎች መረጃ በየመስኩ በፆታና በዕድሜ፣ እንዲሁም በሴቶችና በወንዶች የሚመሩ ኢንተርፕራዞች፣ በተጨማሪም እማወራና አባወራ መለየት፣

## 3.3 የጤና ሴክተር

- የሴቶች ለጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶች ተጋላጭነት ከፍተኛ መሆን በስነ-ተዋልዶ ጤና ላይ የሚያደርሰው ተጽእኖ፤
- የስነ ተዋልዶ አገልግሎት ለሴቶች ተደራሽነቱ፤ የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ተጠቃሚ ወንዶች ማነስ፤

- ከፍተኛ የእናቶች መጠነ ሞት፤
- ሴቶች ወደ ጤና ተቋማት ለመሄድና አገልግሎቱን ለማግኘት የባሎቻቸውን ወይም የቤተቦቻቸውን ፍቃድ ማግኘት የሚያስፈልግ መሆኑ፤
- ሴቶች ጤና አገልግሎቶች የሚከፍሉትን ገንዘብ ማጣት፤
- የጤናን ጉዳይ በተመለከተ በማህበረሰብ ደረጃ በሚቋቋሙ ኮሚቴዎች በዋናነት ወንዶች የሚወከሉበት መሆኑ፤
- በሴቶች ዘንድ ስለ ጤና አገልግሎቶች በቂ መረጃና ተደራሽነት አለመኖር፤

## የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

- ሴቶች ለስልጠና ዕድሎች እኩል ተደራሽ አለመሆን፤
- ሴቶች በጤናው ዘርፍ ከሚሰሩ ሥራዎች ጋር በተያያዘ በዕቅድ፣ በአፈጻጸም ወቅትና በክትትልና ግምገማ ሂደት ውስጥ ያሏቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን፤
- መረጃዎችን ከጾታ አንጻር አጠናቅሮ አለማስቀመጥ

## የመፍትሄ እርምጃዎች

- የእናቶች ሞትን መቀነስ
- የቅድመ ወሊድና ድህረ ወሊድ አገልግሎትን ማጠናከር
- ሴቶች በሰለጠነ የጤና ባለሙያ በጤና ተቋማት እንዲወልዱ በማህበረሰብ ደረጃ ማበረታታት፤
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት ተጠቃሚነት ማሳደግ፤
- በየቀበሌው የጤና ኬላዎችን ተደራሽና ተስማሚ (Friendly) ማድረግ፤
- በቤተሰብ እቅድ ውስጥ የወንዶችን ተሳትፎ ማጎልበት፤
- የጤና ባለሙያዎች በእውቀትና በስነምግባር የታነጸ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤
- የስነ-ተዋልዶ ጤናና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራዎችን አገልግሎት ማጠናከር፤
- ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን (የማህጸን ጫፍና የጡት ካንሰር) ትኩረት በመስጠት ችግሩን ለመከላከልና ለማስወገድ የሚያስችል የተለያዩ ርምጃዎችን መውሰድ፤
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊትን በተመለከተ የግንዛቤ ሥራዎችን በስፋት መሥራት፤

- በገጠር አከባቢ ለሚሰሩ ሴት የጤና ባለሙያዎች ተጨማሪ ማበረታቻዎችን መስጠት፤
- ለጤና ባለሙያዎች በተለይም ሴቶች ላይ በሚፈጸሙ ፆታዊ ጥቃትንና ኤች.አይ ቪ/ኤድስን በተመለከተ ሥልጠና መስጠት፤
- በቤተሰብ ምጣኔ፣ በወሊድ ክትትልና በጤና ተቋማት መውለድ ያላቸውን ጥቅሞችን በተመለከተ የግንዛቤ መስጨበጫ ሥራዎችን መስራት፤

## 3.4 የትምህርት ዘርፍ

### የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

- በሴቶች ትምህርት ዙሪያ የህብረተሰቡ አመለካከት ሙሉ በሙሉ አለመቀየሩ፣ በቤት ውስጥ የስራ ጫናና በሚፈጸምባቸው ጥቃቶች ምክንያት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሴቶች የትምህርት ተሳትፎ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፤
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቅድመ ምረቃ እንዲሁም የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ተሳትፎአቸው እያደገ የመጣ ቢሆንም ከሌሎች የትምህርት እርከኖች ጋር ሲነጻጸር እድገቱ አነስተኛ መሆኑ፤
- በአጠቃላይ በትምህርት ዘርፉ ሴቶችን በውሳኔ ሰጭና በአመራር ቦታዎች በማምጣት የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ ቢሆንም በመካከለኛ እና ከፍተኛ አመራር እርከኖች የሴቶች ድርሻ በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፤
- የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት በሚፈለገው ደረጃ ተደራሽ ባለመሆኑ የሴት ተማሪዎች ተጠቃሚነት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ፤
- በየትምህርት እርከኖቹ የሴቶች ትምህርት ማቋረጥና መድገም፣ የትምህርት ውጤታማነታቸው በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣
- በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህህት ያላቸው ተሳትፎ ካልተማሩ ሴቶች ቁጥር አንጻር ሲመዘን እዉነተኛ መሆን፤
- በሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት መስኮች የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን
- በቴክኒክና ሙያ የሚሰጡ ስልጠናዎች የሴቶችን ፍላጎት ያማከለ አለመሆን፤
- በየደረጃው ባለ የትምህርት እርከኖች የሴት አመራሮች ቁጥር አነስተኛ መሆን
- ሴቶች በዘርፉ በተለያዩ ደረጃዎች ያሏቸው ተሳትፎ አናሳ መሆን፣ በተለይም በአመራር ቦታ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆን፤
- የሴት ተማሪዎች መጠነ ማቋረጡ ከፍተኛ መሆን፤

- በቂ ሴት አስተማሪዎች አለመኖር፤ ሴት አስተማሪዎች ሴት ተማሪዎችን የሚያግዙበት የት/ቤት ስርአት አለመኖር
- በትምህርት ቤቶች ውስጥ እና አከባቢ ለሴቶች ምቹ ሁኔታ አለመኖርና ፆታዊ ጥቃቶችና ትንኮሳዎች መኖር፤
- ከጾታዊ ትንኮሳ ጋር በተያየዘ በትምህርት ቤቶች የሚሰጡ የህይወት ክህሎትና የስነ ልቦና ምክር አገልግሎቶች የተጠናከረ አለመሆን፤
- ያለዕድሜ ጋብቻ ላይ የማህበረሰብ ግፊት፣
- የተለያዩ ስልጠናዎች ለሴቶች ተደራሽ አለመሆን፤

## የመፍትሄ እርምጃዎች

- በየደረጃው ባለ የትምህርት እርከኖችና መስኮች የሴቶችን እኩል ተሳትፎና ውጤታማነት ማረጋገጥ፤
- በየትምህርት ቤቶች ለሴቶች ምቹ ሁኔታ መፍጠር ለምሳሌ የመጸዳጃ ቤቶች መኖር፤
- የትምህርት ማቋረጥና የመድገም ችግሮችን ለመቅረፍ በቤተሰብና በት/ቤት ደረጃ ለሴቶች ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤
- በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሴቶች ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ፤
- የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ማስፋፋትና ማጠናከር፤
- በስራ ላይ የሚገኙ ሴቶችን የትምህርት ደረጃ ለማሻሻል የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የትምህርት እድሎችን በማመቻቸት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- በየደረጃው ባለ የትምህርት እርከኖችና መስኮች በተለይም በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በጥናትና ምርምር ተቋማት የሴት መምህራንን ተሳትፎ ለማሳደግና የውሳኔ ሰጭነትና አመራር ሚናቸውን ለማጎልበት የልዩ ድጋፍ ርምጃ አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ፤
- በገጠር አከባቢ ለሚሰሩ ሴት አስተማሪዎች ተጨማሪ ማበረታቻዎችን (ለምሳሌ መኖሪያ ቤቶችን) መስጠት፤
- ለሴቶች ትምህርት ምቹ ከባቢ መፍጠርና ማሻሻል፤
- ትምህርት ቤቶች ለሴቶች የሚሰጡ የህይወት ክህሎትና የስነ ልቦና ምክር አገልግሎቶችን ማጠናከር፤

- በህጻንነት ያለማግባት ጥቅሞችን በተመለከተ በአከባቢው አርአያ የሚሆኑና በጥሩ ደረጃ የሚገኙ ሴቶችን በማሳተፍ የግንዛቤ መስጨበጫ ሥራዎችን መስራት፤

- በትምህርት ቤቶች በሚቋቋሙ የተለያዩ ኮሚቴዎች ውስጥ የጾታ ስብጥሩን መጠበቅ፤

## 3.5 የኢንዱስትሪ ሴክተር

### የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

- ሴቶች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች የሚጠቀሙበት ክህሎትን እውቀት አነስተኛ መሆን፤
- በማምረቻው ዘርፍ የሴቶቹ ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፤
- ለማምረቻው ኢንዱስትሪዎች ቅድመ አዋጭነት ጥናቶች በሚካሄዱበት ወቅት የሴቶች ተሳትፎ አነስተኛ መሆን፤
- ሴት ባለሀብቶች ለመሳብ የሚደረግ የተለየ ማበረታቻ አለመኖር፤
- በኢንቨስትመንት የምክክር መድረኮች ሴቶች ተሳታፊ እንዲሆኑ የመደገፍ ስራ ዉስንነት፤
- በአገር ውስጥና በውጭ አገር በሚካሄዱ አውደ ርእዮች ላይ የሴቶች ተሳትፎ ለማረጋገጥ የተለያዩ ድጋፎች አለመደረጉ፤
- በሴት አምራቾች የሚመረቱ ምርቶችን ለጥራት ፍተሸ እንዲቀርቡ በማገዝና ደረጃ እንዲወጣላቸው በማድረግ ተወዳዳሪነትን እንዲያጎለብቱ ልዩ ድጋፍ እንዲኖር አልሞ አለመስራት፤
- በግሉ ዘርፍ ኢንቨስትመንት ውስጥ ያሏቸው የሴቶች ተሳትፎ አናሳ መሆን፤
- ለተለያዩ ስልጠናዎች ሴቶች ተደራሽ አለመሆን፤
- ሴት ባለሀብቶች በአገር ውስጥና በውጭ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አለመደረግ፤

### የመፍትሄ እርምጃዎች

- በሥራ ላይ የዋሉ እንዲሁም አዳዲስ የዘርፉን ህጎችና ፖሊሲዎች ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር መቃኘትና ክፍተቶች ካሉ እንዲስተካከሉ ማድረግ፤

- በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር በሚካሄዱ አውደ ርእዮችና ባዛሮች እንዲሳተፉ ሴቶች የተለያዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ ማድረግ፤

- ሴቶችን በብዛት ለሚያሳትፉ ኢንቨስተሮች የተለየ የማበረታቻ ድጋፍ መኖር፤

- የኢንቨስትመንት የምክክር መድረክ ሲዘጋጅ የሴቶችን ተሳታፊነት ማመጣጠን፤

- በኢንቨስትመንት ክትትል የተገኙ ውጤቶችን በጾታ ለይቶ ማደራጀት፤
- በኢንዱስትሪ ሴክተር ውስጥ አዳዲስ ሴቶችን እንዲቀጠሩ ማድረግ፣ የተቀጠሩትንም በአግባቡ እንዲያድጉ ማድረግ፤
- በሴክተሩ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በሥርዓተ-ፆታ ትንተና ዙሪያ፣ በዘርፉ ሴቶችን በሚያበረተቱበትና የስራ ዕድል በሚፈጥሩበት ሁኔታ ላይ ሥልጠና መስጠት፤
- ከሥራ ለተገለሉ ሰራተኞች ሌሎች ስልጠናዎችን መስጠት እንዲሁም የሴፍትኔት ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፤
- በሴት አምራቾች የሚመረቱ ምርቶች ለጥራት ፍተሻ እንዲቀርቡና ደረጃ እንዲወጣላቸው በማድረግ ተወዳዳሪነታቸውን የሚያሳድግ ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ አልሞ መስራትና ከኤጀንሲዎች ጋር ተቀናጅቶ መስራት፤
- በዘርፉ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሴቶችን የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ሲዘጋጅ በቀጥታ እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት፤
- በሴቶች ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶች ጋር አጋርነትን በመፍጠር ሴቶች በኢንዱስትሪ ልማት ውስጥ በላቀ ሁኔታ የሚሳተፉበትን መንገድ መቀየስ፤
- በብሮሹር፣ በንግድ ትርኢት፣ በውጭ ጉብኝት፣ የምርት ማሳያ ቦታ በማዘጋጀትና ድረ-ገጽን በመጠቀም ለሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ምርቶቻቸውን ማስተዋወቅ፤

## 3.6 ውሃና ኢነርጂ

### የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

- የንጹህ ውሃ አቅርቦት አለመኖር፤
- የመስኖና ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክቶች ቀረጻ እስከ ትግበራ ሂደት ውስጥ የሥርአተ-ፆታን ጉዳይን በአግባቡ ከግምት ውስጥ አለማስገባት፤
- አማራጭ ኢኔርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ለሴቶች በበቂ ሁኔታ አለማቅረብ፤
- በውሃ አጠቃቀምና አስተዳደር ሥራዎች ላይ የሴቶቹ ተሳትፎ አናሳ መሆን፤
- አከባቢ ላይ ከሚኖረው ተፅዕኖ አንጻር የሚደረጉ ዳሰሳ ጥናቶች የሥርዓተ-ፆታን ጉዳይ በአግባቡ ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆን፤
- በመልሶ ማቋቋም ፕሮግራሞች የሴቶችን ፍላጎቶችንና ችግሮቻቸውን በአግባቡ አለመረዳት፤

### የመፍትሄ እርምጃዎች

- በገጠር አከባቢ ተመድበው ለሚሰሩ ሴት ባለሙያዎች ማበረታቻዎችን መስጠት፤
- በውሃ ዘርፍ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያና ሴቶችን በውሃ ልማቱ ላይ በሚያሳትፉበት መንገድ በተመለከተ ስልጠናዎችን መስጠት፤
- በውሃ ልማቱ ሥራ ላይ ሴቶች ከመጀመሪያ አንስቶ (ከዲዛይን) ግንባታና ጥገና ድረስ በአግባቡ እንዲሳተፉ ማድረግ፤
- አንዳንድ በአከባቢዎች የሚገኙ አርአያ የሚሆኑ ሴቶችን በመጠቀም ንጽህና አጠባበቅንና የንጹህ ውሃ አጠቃቀም ያላቸውን ጠቀሜታ ለማህበረሰቡ ማስተማር፤

## 3.7 የፍትህ ሴክተር

### የስርአተ ጾታ ጉዳዮች

- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጾታዊ ጥቃቶችን በመከላከልና በማስወገድ ረገድ በማህበረሰቡ ዘንድ የተሟላ የባህሪ/የአመለካከት ለውጥ አለመምጣቱ፤
- የህግ አፈጻጸም ክፍተት መኖርና የተፋጠነ ፍትህ አለማግኘት፤
- ጾታዊ ጥቃትን በሚፈጽሙ አካላት ላይ የሚተላለፉ የቅጣት ውሳኔዎች አስተማሪ አለመሆን፤
- ጥቃት በደረሰባቸው ሴቶች አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ማእከላት በቂ አለመሆናቸውና ያሉትም የተሟላ አገልግሎት አለመስጠት፤
- ነጻ የህግ አገልግሎት ተደራሽ አለመሆን፤

### የመፍትሄ እርምጃዎች

- ሴቶችን ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ከጾታዊ ጥቃቶች መከላከል፤ ጥበቃ ማድረግና ለተጎጂዎች ተገቢ አገልግሎት መስጠትን መሰረት ያደረገ ፕሮግራም ቀርጾ መተግበር፤
- የተቋማትንና የማህበረሰቡን አቅም በመገንባት የመከላከል ስራዎችን ማከናወን፤
- ሴቶች ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ የህግና የፖሊሲ ተፈጻሚነትን ማረጋገጥ፤
- ጥቃት አድራሾች አስተማሪ የሆነ እርምጃ እንዲወስዱ ማድረግና ክፍተት ያለባቸው የህግ ማእቀፎች በየጊዜው በመፈተሽ ማሻሻል፤

- በኅጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ጥቃቶች ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሴቶች ዘርፈ ብዙ፣ ጥራቱን የጠበቀ እና በቀላሉ ተደራሽ የሆነ የህግ ከለላና ነጻ የህግ አገልግሎት ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ፤ የጤና፣ የማህበራዊና የስነልቦና ድጋፎችን በአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤

- የመጠለያና ሌሎች መሰረታዊ አገልግሎት የሚሰጡ ተሀድሶ ማእከላትን በመገንባት ሴቶች በዘላቂነት ስብእናቸው እንዲስተካከል የማድረግ ቅንጅት ስራዎችን መስራት፤

## 3.8 ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን

### የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮች

- በግምባታው ዘርፍ የተሰማሩ ሴቶች ብዛት እጅግ አናሳ መሆን፤

- በዘርፉ ለተሰማሩ ሴቶች የሚደረግ ድጋፍ አነሳ መሆን፤

- የሥራ ዕድል ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ በአግባቡ ከግምት ውስጥ አለማስገባት፤

- ለሥርዓተ-ፆታ ጉዳይ ምላሽ ለመስጠት በቂ በጀት አለመመደብ፤

- በግንባታው ዘርፍ ሴቶች አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የሚያግዙ ስልጠናዎች በበቂ ሁኔታ አለመሰጠት፤

### የመፍትሄ እርምጃዎች

- በሥራ ላይ የዋሉ እንዲሁም አዳዲስ የዘርፉን ህጎችና ፖሊሲዎች ከሥርዓተ-ፆታ አንጻር መቃኘትና ክፍተቶች ካሉ እንዲስተካከሉ ማድረግ፤

- በዘርፉ የሚሰሩ ሴት ሰራተኞችን በስፋት መቅጠር እንዲሁም በአግባቡ ዕድገት መስጠት፤

- በከተማ ልማት ውስጥ ለሚሰሩ ባለሙያዎች በሥርዓተ-ፆታ ዙሪያና ሴቶችን በከተማ ልማቱ ላይ በሚያሳትፉበት መንገድ በተመለከተ ስልጠናዎችን መስጠት፤

- ሴቶችን በከተማ ፕላን፣ በዲዛይን፣ መሰረተ-ልማቶች ዝርጋታ፣በግምባታው ዘርፍ በሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች ላይ እንዲሁም በሌሎች የጥገና ሥራዎች ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ማድረግ፤

- በአከባቢዎች የሚገኙ አርአያ የሚሆኑ ሴቶችንና ሌሎች ሰዎችንም በመጠቀም የከተማ ንጽህና አጠባበቅንና ሌሎች የልማት ስራዎችን በተመለከተ ህብረተሰቡን ማስተማር፤

Ministry of Finance (MoF)